# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 106 ታኅሣሥ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ሆቴሎቹ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔ እንግዶችን ለማስተናገድ ተዘጋጅተዋል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- ለ37ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔ የሚመጡ እንግዶችን ለማስተናገድ ሙሉ ዝግጅታችንን አጠናቀናል ሲሉ በአዲስ አበባ የሚገኙ ባለኮከብ ሆቴሎች ገለጹ፡፡

በኢትዮጵያ ስካይ ላይት ሆቴል የሽያጭ ክፍል ሃላፊ አቶ አየሁ ገሰሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅ እንደገለጹት፤ በሀገራችን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔም ሆነ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች መካሄዳቸው ለሆቴል ዘርፉ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡

እነዚህ ኩነቶች ከፍተኛ ሃላፊነት ላይ ያሉ ሰዎችን የሚያሳትፉ በመሆናቸው ሆቴሎች በአገልግሎት አሰጣጥ ኢትዮጵያን የሚያስተዋውቁበት እድል ይፈጥራሉ ያሉት አቶ አየሁ፤ በተጨማሪም በሀገራችን ያሉ ሆቴሎች ያሉበትን ደረጃ የምናሳይበት ነው ብለዋል፡፡

እንግዶችን ለማስተናገድ ብዙ ዝግጅት ያስፈልጋል ያሉት አቶ አየሁ፤ በዚህም ስካይ ላይት ሆቴል ለ37ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔ ለሚመጡ እንግዶች የተሟላ አገልግሎት ለመስጠት ከወዲሁ ዝግጅቱን አጠናቋል ሲሉ

ሆቴሎቹ የአፍሪካ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## የኢትዮጵያ አየር ኃይል ለአፍሪካ አየር ኃይሎች አብነት የሚሆን ሥራ ሠርቷል

ገጽ 4








## “የሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ መደጋገፍ ለብዙ የሀገሪቱ ችግሮች መፍትሄ ይሰጣል”

\- የሀገር ሽማግሌ ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ

መስከረም ሰይፉ

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ መደጋገፍ ለብዙ የሀገሪቱ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥ መሆኑን የሀገር ሽማግሌ የሆኑት ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ገለጹ፡፡

“የሀገራዊ ምክክርና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ገበታውን ከማህበረሰቡ የጀመረው የወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት

ፋንታነሽ ክንዴ

ኢትዮጵያ በተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶች የታደለች ሀገር ናት። እንዳለመታደል ሆኖ ካላት ሀብት ይልቅ ድህነት ዋነኛ መለያዋ ሆኖ ዘመናትን ተሻግሯል። ይህ እውነት ያንገበገባቸው የሀገር ልጆች ድህነትን ታሪክ ለማድረግ መታተር ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

ባለፉት ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ሃሳብ አመንጭነት ‹‹ገበታ ለሀገር›› እና ‹‹ገበታ ለትውልድ›› በሚል መሪ ሃሳብ የተለያዩ ፕሮጀክቶች በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተገነቡ ይገኛሉ። ይህም ‹የጋን ውስጥ መብራት› ሆነው የነበሩ ብዙ ሀብቶች እንዲታዩ ዕድል ፈጥሯል። በዚህ ሂደት እየተገነቡ ካሉ ፕሮጀክቶች የወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት አንዱ ነው።

ገበታውን ከማህበረሰቡ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - በሪሁን ታደሰ









አቶ ባንጉ በቀለ

# በክልሉ ከበጋ መስኖ ልማት ከ15 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል

- ከ68 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ለማልማት ታቅዷል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮው የምርት ዘመን ከበጋ መስኖ ልማት ከ15 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ወደ ሥራ መገባቱን የሲዳማ ክልል እርሻ ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ፡፡ ከ68 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ለማልማት ታቅዷል፡፡

የቢሮው ምክትልና የእርሻ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ባንጉ በቀለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮው የምርት ዘመን በክልሉ ከሚለማው ከ68 ሺህ 978 ሄክታር መሬት ከ15 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

እንደ አቶ ባንጉ ገለጻ፤ የበጋ መስኖ ልማት ሥራው በሁለት ዙር የሚለማ ሲሆን በመጀመሪያ ዙር 55 ሺህ ሄክታር እንዲሁም በሁለተኛ ዙር 13 ሺህ 978 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፡፡

ከሚለማው ከ68 ሺህ 978 ሄክታር ውስጥ 7 ሺህ 250 ሄክታር መሬት የበጋ መስኖ ስንዴ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው፤ በአጠቃላይ 297 ሺህ 250 ኩንታል የስንዴ ምርት ይጠበቃል ብለዋል፡፡

በበጋ መስኖ ልማት በዋናነት ስንዴን ጨምሮ አቡካዶ፣ ፓፓያ፣ ፍራፍሬ፣ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች እንዲሁም በቆሎ በስፋት እንደሚለማ ጠቅሰው ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ጥሩ መሻሻሎች መኖሩን አስረድተዋል፡፡

ባለፈው የምርት ዘመን በበጋ መስኖ ልማት ሥራው ላይ የምርጥ ዘር አቅርቦት እጥረት፣ የባለሙያዎች የግንዛቤ ክፍተት፣ ሥራው ወቅቱን ጠብቆ አለመጀመር እንዲሁም ምርቱ ለተፈጥሯዊ አደጋዎች መጋለጥ በምርት ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን አቶ ባንጉ ገልጸዋል፡፡

ያጋጠሙ ክፍተቶችን በመሙላትና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን በማከናወን የዘንድሮው የበጋ መስኖ ልማት ሥራው ከጥቅምት ወር ጀምሮ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

የበጋ መስኖ ልማት መካናይዜሽን የእርሻ መሣሪያዎችንና ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

የበጋ መስኖ ልማት የአርሶ አደሮች ኑሮ እንዲሻሻልና ገቢያቸው እንዲጨምር ማድረጉን የጠቆሙት ኃላፊው፤ በቀጣይ የበጋ መስኖ ልማት ውጤታማ እንዲሆን በልዩ ትኩረት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

ሥራው በሚፈለገው መጠን ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግም በተለይም ከክልሉ ውሃና ማዕድን እንዲሁም ንግድ ቢሮና ሌሎችም ተቋማትና ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት እየተሠራ እንደሆነም አስታውቀዋል፡፡

# በግብር ላይ የሚፈጸሙ ማጭበርበሮችን ለመከላከል የንግዱ ማኅበረሰብ ሊተባበር ይገባል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- ከተማዋ ትክክለኛ ገቢ እንድታገኝ ለማስቻል የንግዱ ማህበረሰብ በግብር ላይ የሚፈጸሙ ማጭበርበሮችን እንዲከላከል ጥሪ ቀረበ፡፡

ከተማ አስተዳደሩ የንግድ ማኅበረሰቡን ሰሞኑን ባወያየበት ወቅት እንደገለጸው፣ ከተማዋ ከግብር የምታገኘው ገቢ ከጊዜ ወዲጊዜ እየጨመረ የመጣ ቢሆንም፣ በግብር ላይ የሚፈጸሙ ማጭበርበሮች በከተማዋ ከሚካሄዱ ግብይቶች አንጻር ከተማ አስተዳደሩ ትክክለኛ ገቢ እንዳይሰበስብ አድርጎታል፡፡



አቶ አደም ኑሪ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ አደም ኑሪ ግብር የሀገርን መሠረተ ልማት ለማሻሻልና ለነዋሪው ምቹ ሀገርን ለመገንባት ዋነኛው የገቢ ምንጭ መሆኑን አንስተው፣ አብዛኛው ነጋዴም ግብሩን በአግባቡ የሚከፍልና የሕግ የበላይነትን የሚያከብር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

ይህ ቢሆንም፣ ከዚህ በተቃራኒ በሐሰተኛ ደረሰኝ ግብይት የሚፈጽሙ፣ ከዋጋ በታች የሚሸጡና፣ ግብር የሚያጭበረብሩ ሕገ ወጥ ነጋዴዎች አሉ ያሉት ኃላፊው፣ እንዲህ ያለው የአቋራጭ ተጠቃሚነት አስተሳሰብና ተግባር እንደ ሀገር ኢኮኖሚያችንን የሚጎዳና የፍትሐዊ ተጠቃሚነት መርህን የሚጻረር በመሆኑ ሕግን አክብሮ እየሠራ ያለው ነጋዴ ይህንን ሕገ ወጥ ተግባር በመከላከል በኩል ከመንግሥት ጎን እንዲቆም ጠይቀዋል፡፡

በመንግሥት ረገድ በሲስተምና ጥብቅ ፍተሻን በማድረግ ሕገ ወጥ ደረሰኝን ለመከላከል ጥረት እያደረገ እንደሆነ የጠቆሙት ኃላፊው፣ ከሚያገኘው ገቢ የሚጠበቅበትን የሚከፍለውና የሕግ የበላይነትን አክብሮ የሚሠራው የንግዱ ማኅበረሰብ፣ ሐሰተኛ ደረሰኝ እንዳይቀበልና ያልበላውን እንዳይከፍል የራሱን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

መንግሥትና ግብር ከፋዩ እርስ በእርሱ እንደተጋመደ ሸማ ነው ያሉት ኃላፊው፣ በገቢ፣ በልማት፣ በሠላምና ተያያዥ ጉዳዮች ስኬት ማስመዝገብ የሚቻለው ሁለቱ አካላት በትብብር ሲሠሩ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

መዲናዋ በማኅበራዊና በኢኮኖሚ ዘርፍ በተለይም ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ጀምራ ማጠናቀቅ የቻለችው ከህብረተሰቡ በተሰበሰበ ግብር ነው ያሉት አቶ አደም፤ የንግዱ ማኅበረሰብ መንግሥትን ከተባበረና የግብር ማጭበርበሮችን መከላከል ከተቻለ የከተማዋን ገቢ አሁን ካለበት ማሳደግና በርካታ የመሠረተ ልማት ሥራዎችን ማሳካት ይቻላል ብለዋል፡፡

ለከተማዋ የልማት ስኬት ነጋዴው ማህበረሰብ ከከተማ አስተዳደሩ ጋር በቅንጅት እንዲሠራም አሳስበዋል፡፡



# በጂግጂጋ በአንድ ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ወጪ የተለያዩ ግንባታዎች እየተከናወኑ ነው

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በጂግጅጋ ከተማ ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የመሠረተ ልማትና የተለያዩ የኢንቨስትመንት ግንባታዎች እየተከናወኑ መሆኑን የከተማዋ ከንቲባ ዚያድ አብዲ (ኢ/ር) ገለጹ። በከተማዋ የሚገነቡ 34 ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገዶች በ2016 በጀት ዓመት እንደሚጠናቀቁም ተናግረዋል፡፡

ከንቲባ ዚያድ አብዲ (ኢ/ር) በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በጂግጂጋ ከተማ ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ የመንገድ፣ የኢንቨስትመንት፣ ለአረንጓዴ ልማትና ለሥራ ዕድል ፈጠራ የሚረዱ ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ይገኛል።

ከለውጡ ወዲህ በጅግጅጋ ከተማ የከተማ ማስተር ፕላንና ካዳስተር ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቁመው፤ በጂግጂጋ ከተማ የሚገነባው 34 ኪሎ ሜትር የአስፓልት መንገድ በመጠናቀቅ ላይ በመሆኑ በተያዘው ዓመት መጨረሻ አገልግሎት መስጠት እንደሚጀምር አመላክተዋል፡፡

የከተማውን ወጣት በተለያዩ ዘርፎች በማሰማራት የሥራ አጥን ቁጥር ለመቀነስ የሚያስችሉ ሥራዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ የሥራ እድል ለመፍጠር የሚረዱ ሼዶች እየተገነቡ መሆኑን ጠቁመዋል።

ጂግጂጋን በአረንጓዴ ልማትና ውበት ተመራጭ ከተማ እንድትሆን የሚያስችሉ ሥራዎች በተቀናጀ መልኩ ከህብረተሰቡ ጋር እየተከናወነ መሆኑን ተናግረዋል።

ጂግጂጋ ከተማን ለነዋሪዎች ምቹና የኢንቨስትመንት ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በአሁኑ ጊዜ ከተማዋ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ እንተከናወነባት እንደሚገኝ አስረድተዋል፡፡

በክልሉ በመጣው አንጻራዊ ሰላም በርካታ ኢንቨስተሮች ወደ ጂግጂጋ በመምጣት ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ በአሁኑ ወቅት ከ600 መቶ ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ 18 ኢንቨስተሮች ወደ ሥራ በመግባት ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ከንቲባው እንዳመላከቱት፤ በከተማዋ ኢንቨስትመንት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች በሁለገብ የገበያ ማዕከላትና በሆቴል ዘርፍ ተሰማርተዋል፡፡ በከተማው የመጣው ሰላማዊ የንግድ እንቅስቃሴ ከተማዋን ለኢንቨስትመንት ተመራጭ አድርጓታል።

በከተማዋ በመገንባት ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች በፌዴራል፣ በክልሉና በከተማ አስተዳደሩ በጀት የሚከናወኑ መሆናቸውን የተናገሩት ከንቲባው፤ ህብረተሰቡ ለመሠረተ ልማት ግንባታዎች ውጤታማነት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን ጠቁመዋል።

# ሚኒስቴሩ ዘመናዊና ተደራሽ የንግድ አሠራር ሥርዓትን ለማረጋገጥ እየሠራ ነው

## - ከአንድ ሚሊዮን በላይ ደንበኞች በኦንላይን አገልግሎት አግኝተዋል

**አማን ረሺድ**




አዲስ አበባ፡- የንግዱን ማህበረሰብ ውጣ ውረድ ማስቀረት የሚያስችል ዘመናዊና ተደራሽ የንግድ አሠራር ሥርዓትን ለማረጋገጥ እየተሠራ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በአምስት ወራት ውስጥ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ደንበኞች በኦንላይን አገልግሎት ማግኘታውንም አስታውቋል፡፡

በሚኒስቴሩ የኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ በላይነሽ ረጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የንግዱን ማህበረሰብ ውጣ ውረድ ማስቀረት የሚያስችል ዘመናዊና ተደራሽ የንግድ አሠራር ሥርዓትን ለማረጋገጥ አየተሠራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ ገለጻ፤ በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት ውስጥ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ደንበኞች በኦንላይን አገልግሎት ማግኘት ችለዋል፡፡

ባለፉት አምስት ወራት በፌዴራልና በሁሉም ክልሎች የኦንላይን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መሰጠቱን ጠቅሰው፤ አንድ ሚሊዮን አስራ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ አስራ አምስት ደንበኞች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ሆነዋል ብለዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ አምስት ወራት አሮሚያና አዲስ አበባ ደንበኞችን በማስተናገድ ቀዳሚውን ደረጃ መያዛቸውን ጠቁመዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የደንበኞችን እንግልትና ውጣ ውረድ በማስቀረት ዲጅታል ኢትዮጵያ 2025ን እውን ለማድረግ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠራ እንደሚገኝ ሥራ አስፈጻሚዋ አስረድተዋል፡፡

የንግድ ሥርዓቱን በዘመናዊ መንገድ ለመምራት ከፌዴራልና ከአዲስ አበባ ገቢዎች፣ ከንግድ ባንክ ከኢትዮ ቴሌኮምና ከሌሎች 16 ባንኮች እንዲሁም ከመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን ጋር በጋራ እየሠራ ይገኛል ብለዋል፡፡

የንግድ ምዝገባና ፍቃድ ሥርዓትን ዲጂታል ማድረግ፣ በአንድ ቦታ የሚሰጡ አገልግሎቶችና የንግድ ፍቃድ አሰጣጥ ሂደቶች እንዲሻሻሉ ሰፊ ሥራ መሠራቱን ገልጸው፤ የኦንላይን አገልግሎት አሰጣጡ ከበፊቱ የተሻለ አፈጻጸም ተመዝግቧል ብለዋል፡፡

ችግሮች ሲያጋጥሙ ቀልጣፋ ድጋፍና ክትትል እየተደረገ ሲሆን ተጨማሪ ድጋፍ ሰጪ ሲስተም በማልማት ወደ ተግባር ለማስገባት በትኩረት እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

በቀጣይ በሀገር አቀፍ ደረጃ በበይነ መረብ የሚሰጠውን የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት አሰጣጥ ሽፋን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

የንግዱ ማህበረሰብ ያለምንም እንግልት ባለበት ቦታ ሆኖ በቀረቡት የመክፈያ መንገዶች በመጠቀም ፍቃዱን እንዲያድስ ብሎም ምዝገባ እንዲያከናውን ሥራ አስፈጻሚዋ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



አቶ ሓፍታይ ገብረእግዚአብሔር

# በመዲናዋ በቱሪዝም ዘርፍ ከ17 ቢሊዮን ብር በላይ ተንቀሳቅሷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት በመጀመርያው ሦስት ወራት ውስጥ በመዲናዋ በቱሪዝም ዘርፍ 17 ቢሊዮን 250 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ መንቀሳቀሱንና ወደኢኮኖሚው ፈሰስ መደረጉን የአዲስ አበባ ባህል ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ከተማ ባህል፣ ኪነ ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሓፍታይ ገብረእግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በሩብ ዓመቱ 268 ሺህ 80 የሚሆኑ የውጭ ሀገራት ጎብኚዎች ከተማዋን ጎብኝተዋል።

በበጀት ዓመቱ በመጀመሪያው ሩብ ዓመት የከተማው ቱሪዝም የተሻለ መነቃቃት ታይቷል ያሉት አቶ ሓፍታይ፤ የተገኘው ውጤት በገቢና በቱሪስት ፍሰት ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል ብለዋል። በከተማው የቱሪስቶች ቆይታ ለማድረግ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በከተማዋ በቱሪዝም ዘርፍ ያለውን ሀብት ወደ ኢኮኖሚ ቀይሮ ለመጠቀም በዘርፉ ያሉ ችግሮች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የቱሪዝም ዘርፉ ለከተማው ኢኮኖሚ መነቃቃት ጉልህ አስተዋጾ እያበረከተ እንደሚገኝም ኃላፊው ተናግረዋል።

በከተማው እየተገነቡ የሚገኙ ሰፋፊ መሠረተ ልማቶች ለከተማው ቱሪዝም ዘርፍ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው ያት አቶ ሓፍታይ፤ በተለይ የዓድዋ ሙዚዬምና የአፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር ለዘርፉ ተጨማሪ እድል እንደሚፈጥሩ ገልጸዋል።

በተጨማሪም በከተማው የተገነቡ ፓርኮችና የመዝናኛ ሥፍራዎች ዋነኛ የቱሪስት መስህብ እየሆኑ እንደሆነ ጠቁመው፤ የቱሪዝምን ኢኮኖሚ እያሳደጉ እንደሚገኙም አመላክተዋል።

እንደ አቶ ሓፍታይ ገለጻ፤ ቱሪዝምን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከማስተዋወቅ አንጻር ውስንነቶች አሉ። ይህንን ችግር ለመቀነስ በቀጣይም በአፍሪካ ህብረት ጉባዔ ላይ ቱሪዝምን ለማስተዋወቅ በከንቲባዋ የሚመራ ኮሚቴ ተዋቅሮ የቱሪዝም ማዕቀፍ እየተዘጋጀ ነው ብለዋል።

# በሸገር ከተማ ዲጂታል የመሬት መረጃ አያያዝ ሥርዓት ሊተገበር ነው

## - 604 የኢንቨስትመንት ፈቃዶች ተሰርዘዋል

**ማርቆስ በላይ**




ፎቶ - ገበዘ ገብሬ

ዶክተር ተሾመ አዱኛ

አዲስ አበባ፡- በሸገር ከተማ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዲጂታል የመሬት መረጃ አያያዝን ሥርዓት ሊተገበር መሆኑን የከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ። በከተማው 604 የኢንቨስትመንት ፈቃድ ስምምነቶች መሰረዛቸው ተገልጿል።

የሸገር ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ተሾመ አዱኛ (ዶ/ር) በከተማው የኢንቨስትመንት ተግባራት ዙሪያ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ በከተማው በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመሬት መረጃ አያያዝ ሥርዓት ተግባራዊ ሊደረግ ነው።

የዲጂታል መረጃ አያያዝ ሥርዓቱ ሕገወጥ አሠራሮችን ለመቅረፍና የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ግንባታን ለማከናወን የሚረዳ መሆኑን ከንቲባው አስተድተዋል።

ባለፉት ጊዜያት የከተማውን የመሬት መረጃን አያያዝ በቴክኖኖሎጂ የማደራጀት ሥራ መሠራቱን የገለጹት ከንቲባው፤ በአሁኑ ወቅት የከተማው የኢንቨስትመንት ፈቃድ አሰጣጥ በኦንላይን የሚከናወንበት መተግበሪያ ተዘጋጅቷል ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ ፈቃዳቸው አምስት ዓመት ያለፋቸውን የግንባታ ሂደቶችን፣ የኢንቨስትመንት መሬትን በማከራየትና፣ ባዶ መሬት ይዘው በተቀመጡ ኢንቨስተሮች ላይ ርምጃ መወሰዱን በመግለጽ፤ በተወሰደው ርምጃ 604 የኢንቨስትመንት ፈቃዶች መሰረዛቸውን አስታውቀዋል።

ርምጃ ከተወሰደባቸው ኢንቨስትመንቶች 510 ሄክታር መሬት ተመላሽ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ አንድ ሺህ 602 ኢንቨስትመንቶች ግንባታቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ እንዲገቡ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጣቸው አስረድተዋል፡፡

በከተማው ያለፈቃድ ትርፍ መሬት የያዙ አንድ ሺህ 32 ባለሀብቶች ላይ ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወሰድ በመግለጽ፤ መሬትን በኪራይ የያዙ 395 ባለሀብቶችን ወደ ሊዝ አሠራር ለመመለስ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

ከተማው ከመደራጀቱ በፊት ፈቃድ ከወሠዱ አራት ሺህ 812 ኢንቨስትመንቶች መካከል ወደ ሥራ የገቡት ከሁለት ሺህ አይበልጡም ያሉት ከንቲባው፤ ከተማው ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ የህብረተሰቡን ችግር የሚቀርፉና ሕግን የተከተሉ በርካታ የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች ተግባራዊ እየተደረጉ መሆኑን ተናግረዋል።

የሸገር ከተማን ለኑሮ ምቹ በማድረግ ለመገንባት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይም ማህበረሰቡን መሠረት ያደረጉ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛል ብለዋል።

በከተማው ያለውን የመሬት አስተዳደር ችግር ለመቅረፍ እየሠራን ነው ያሉት ዶክተር ተሾመ፤ ከተማ አስተዳደሩ ኢንቨስት ለማድረግ ለሚመጡ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

በተጨማሪም ከተማ አስተዳደሩ ለባለሀብቶች ድጋፍ ለመስጠትና ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በተለይም በንግድ ማዕከላት፣ ኢንዱስትሪ፣ ሆቴልና ሪዞርት፣ ግብርና ማቀነባበሪያ፣ አይሲቲና ቱሪዝምን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ለሚሳተፉ አልሚዎች አስፈላጊው ድጋፍ ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

# ክልሉ በ2016/17 የምርት ዘመን 62 ሺህ ሄክታር መሬት በሜካናይዜሽን ለማረስ ታቅዷል

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል በክልሉ በ2016/17 የምርት ዘመን 62 ሺህ ሄክታር መሬት በሜካናይዜሽን ለማረስ እንደታቀደም የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ ፡፡

የጋምቤላ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ የግብርና ሜካናይዜሽንና ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ኡጉታ ኡኩኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልል ደረጃ ግብርናን የማዘመን ሥራዎች በስፋት እየተሠሩ ሲሆን፤ በዚህም አርሶአደሩ ትራክተር እንዲደርሰው የከተማ አስተዳደሩን ሳይጨርምር በክልሉ ወስጥ ለሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች እያንዳንዳቸው አራት ትራክተር ተሰጥቷቸዋል፡፡ እነዚህም የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

በዘንድሮው ዓመት በፌዴራል መንግሥት አማካኝነት በሚደረገው ግዥ ቁጥሩ ከዚህ ከፍ እንደሚል ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮው ዓመት በሁሉም ወረዳዎች በተለይ በክላስተር የሚያመርቱ አርሶአደሮች የግብርና ሥራቸውን እንዲያዘምኑና በግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ላይ ልዩ ትኩረት እንዲያገኙ በስፋት እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ በክልሉ በ2016/17 የምርት ዘመን 62ሺህ ሄክታር መሬት የግብርና ሜካናይዜሽን አገልግሎት ይሰጣል ተብሎ መታቀዱንም ዳይሬክተሩ ገልጸዋል፡፡ ይህንን ለማሳካት የአርሶ አደሩን ፍላጎት መሠረት ያደረገ የንቅናቄ ዝግጅት እየተደረገ እንዳለም አስታውቀዋል፡፡

ግብርናውን ለማዘመን በተለይ ትራክተሮች በሚደርሱባቸው ቦታዎች በሙሉ አርሶ አደሩ እንዲጠቀምበት ተደርጓል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ባለፈው ዓመት ለወረዳዎች ከታደሉት 36 ትራክተሮች በተጨማሪ በዘንድሮው ዓመትም ክልሉ 14 አዳዲስ ትራክተሮችን እንዳስገባ ተናግረዋል፡፡ በክልሉ ባሉ 13 ወረዳዎችና አንድ የከተማ አስተዳደር እንዳሉ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ ምርት ሊመረትባቸው የሚችሉና በከፍተኛ ደረጃ መሬት ያላቸውን ወረዳዎች የሜካናይዜሽን ግብርናን በስፋት ተግባራዊ እንዲያደርጉ እየተሠራ እንዳለ አመልክተዋል፡፡

በተጨማሪም በክልል ማዕከል አስራ ስምንት ያህል ትራክተሮች እንዳሉና እነዚህ ትራክተሮች ድጋፍ ለሚፈልጉ አካላት በተለይም ለመከላከያ ሠራዊት መዋል እንደሚችሉ ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል፡፡

ዳይሬክተሩ አክለውም፤ በክልሉ ምርት የማምረት ሥራው በአራት ወቅቶች እንደሚከናወኑ ጠቅሰው፤ በ2015/16 የምርት ዘመን በአየር መዛባትና በነበረው የጸጥታ ችግር በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የግብርና ሥራው ተስተጓጉሎ እንደነበር አንስተዋል፡፡

በተደረጉ የሠላም ውይይቶች በአሁኑ ወቅት ውስጣዊ የጸጥታ ችግር እየተረጋጋ መምጣቱን ገልጸው፤ ይህም ቀጣይ የግብርናውን ሥራ በስፋት ለማከናወን ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል፡፡ የክልሉ ሠላም በዚሁ ከቀጠለ በተሻለ የግብርና ሥራ የተሻለ ምርት ሊመረት እንደሚችል ነው ያሳወቁት፡፡

# የኢትዮጵያ አየር ኃይል ለአፍሪካ አየር ኃይሎች አብነት የሚሆን ሥራ ሠርቷል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር ኃይል በቴክኖሎጂ፣ በሰው ኃይልና በመሠረተ ልማት እየገነባ ያለው አቅም ለአፍሪካ አየር ኃይሎች ትምህርት የሚሰጥ መሆኑን የተለያዩ ሀገራት ወታደራዊ አታሼዎች ገለጹ።

የሴኔጋል ወታደራዊ አታሼ ሌተናል ኮሎኔል ማማዱ ፉል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ሁሌም በአፍሪካ የሰላም ማስከበር ተግባር ግንባር ቀደም ተሰላፊ ናት። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ አየር ኃይሎች የአብራሪዎች ሥልጠና እና የአውሮፕላን ጥገና አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች። ይህም የአፍሪካ አየር ኃይል አቅምን የወደፊት ተስፋ ያሳያል።



ሌተናል ኮሎኔል ማማዱ ፉል

የኢትዮጵያ አየር ኃይል በቴክኖሎጂ፣ በሰው ኃይልና በመሠረተ ልማት እየገነባ ያለው አቅም ለአፍሪካ አየር ኃይሎች ትምህርት የሚሰጥ ነው ያሉት ሌተናል ኮሎኔል ማማዱ፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ጋር በመተባበር ያካሄደው የጥቁር አንበሳ የአየር ትርዒት የኢትዮጵያ የመከላከል አቅም የደረሰበትን ደረጃና ስኬት ያሳያል ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአየር ኃይሏን ለማዘመን የምታደርገው ጥረት ሁሉንም አፍሪካውያን የሚያኮራ፣ የሰላም ዋስትና የሚሰጥ እና ሀገሪቷ አህጉራዊ መረጋጋትን ለማረጋገጥ ያላትን ዝግጁነት ያሳያልም ነው ያሉት ሌተናል ኮሎኔል ማማዱ።



ሜጀር ጀነራል ሄንድሪክ ቱቱ

ሌተናል ኮሎኔል ማማዱ ፉል 88ተኛውን የኢትዮጵያ አየር ኃይል የምሥረታ በዓልን ምክንያት በማድረግ የአፍሪካ አየር አዛዦች ፎረም መዘጋጀቱን ገልጸው፤ ፎረሙ በሀገራት መካከል የእውቀት ልውውጥና የአቅም ግንባታ ትምህርቶችን እንዲወስዱ ከማስቻሉ ባሻገር በተሳታፊዎች መካከል ያለውን ወዳጅነት እና ትብብር ለማሳደግ እንደሚረዳ ተናግረዋል።

የቦትስዋና አየር ኃይል ጦር ዋና አዛዥ ሜጀር ጀነራል ሄንድሪክ ቱቱ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የአፍሪካ አየር ኃይሎችን አንድ ለማድረግ እና የአጋር አካላትን አቅምና ክፍተቶች በመለየት ለኋለኛው ችግሮች መፍትሄዎችን በማዘጋጀት ትልቅ ሥራ እየሠራች ነው ብለዋል።

የአፍሪካ አየር ኃይል አዛዦች ፎረም የአፍሪካ አየር ኃይል አብራሪዎችን፣ ቴክኒሻኖችን እና ሌሎች ባለሙያዎችን አቅም በጋራ ለማሳደግ የሚያስችል የግንኙነት እና የልምድ ልውውጥ መድረክ ይፈጥራል ያሉት ሜጀር ጀነራል ሄንድሪክ፤ የጋራ ችግሮቻችንን እና ስጋቶቻችንን ለመቅረፍ በአካባቢው ትብብራችንን ማጠናከር አለብን፤ ምክንያቱም አጋርነታችን ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካ መፍትሄዎች መፍጠር አለበት በማለት ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ፓይለቶች በጥቁር አንበሳ የአየር ትርዒት ያሳዩት ችሎት የሚደነቅ ነው ያሉት ደግሞ የሩሲያ መከላከያ አዛዥ ኮሎኔል አሌክሳንደር ፓኔቪን ናቸው።

እንደ ኮሎኔል አሌክሳንደር ገለፃ፤ ኢትዮጵያ በአቬየሽን ዘርፍ እየሠራች ያለውን ሥራ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር መሥራቷን አጠናክራ መቀጠል አለባት። የአፍሪካ አየር ኃይል ኃላፊዎችና ከፍተኛ አመራሮች፣ ኩባንያዎች፣ ባለሙያዎች እና ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት የተገኙበት ፎረም መካሄዱ አፍሪካ በአቪየሽን ዘርፍ ከፍተኛ ስኬት እንድታስመዘግብ ይረዳል ብለዋል።

# ገበታውን ከማህበረሰቡ...

የወንጪ ደንዲ የኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ ዳባ ጂንፌሳ እንደሚሉት፤ ወንጪ ሀይቅና አካባቢው ተፈጥሮ አብዝታ ተጠባበታለች። ሆኖም ሀብቱ አስታዋሽ ባለማግኘቱ ለአካባቢው ማህበረሰበም ሆነ ለሀገር ማበርከት የሚገባውን አስተዋጽኦ ሳያበረክት ቆይቷል። ዛሬ ግን ያ ታሪክ ተቀይሮ አካባቢው ላይ ደረጃቸውን የጠበቁ ሎጆች፣ ቪላና መኝታ ቤቶች ተገንብተዋል።

አቶ ዳባ እንደሚሉት፤ ቦታው ጎብኚዎች ተደስተው የሚሄዱበት ብቻ ሳይሆን የአካባቢው ማህበረሰብ ተጠቃሚ ማድረግ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ተሠርቷል።

በዚህም በፕሮጀክቱ ግንባታ ተነሺ ለሆኑ 13 አርሶ አደሮች ደረጃቸውን የጠበቁ መኖሪያ ቤቶች ከነሙሉ ቤት ዕቃቸው ተገንብቶ የተሰጣቸው ሲሆን፣ ለጎብኚዎች እያከራዩ ኑሯቸውን የሚደጉሙባቸው ክፍሎችም ተሠርተውላቸዋል።

ይህም ጎብኚዎች የአካባቢውን ተፈጥሮ አድንቆ ከመመለስ ባሻገር የማህበረሰቡን ቱባ ባህሎች እንዲገነዘቡ ዕድል የሚፈጥር ነው። ይህ ፕሮጀክት የአካባቢውን ማህበረሰብ የበይ ተመልካች የማድረግ ባህልን ከመሠረቱ ቀይሯል ይላሉ።

እንደ አስተባባሪው ገለጻ፤ ኢኮ ቱሪዝሙን ተፈጥሮውን ጠብቆ ምርጥ የቱሪስት መስህብ ለማድረግ የመዝናኛና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ተከናውነውለታል።

ከወንጪ ሐይቅ ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ 42 ኪሎ ሜትር መንገድ ፣ የኤሌክትሪክ፣ የአትሌቶች ረዥም ርቀት መሮጫ ትራክ፣ ካፍቴሪያዎችን፣ ባህላዊ ምግብ ቤቶች፣ በሐይቁ ዳርቻ የተለያዩ መዝናኛ ቦታዎች ተገንብተው ለአካባቢው ተጨማሪ ድምቀትም፤ ሀብትም ሆነዋል።

በተጨማሪም የአካባቢውን የተፈጥሮ ጸጋ የሆነውን የማር ምርት መሸጫ፣ የባህል ቤት፣ 200 መኪናዎችን የሚያስተናግድ የመኪና ማቆሚያና የመግቢያ በሮችም የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኚዎችን በመጠባባቅ ላይ ናቸው።

በፕሮጀክቶች ግንባታ ሂደት ለብዙ ዜጎች የእለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ መፍጠሩን የሚጠቅሱት አቶ ዳባ፤ በቀጣይነትም ቦታውን በማስጎብኘትና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችንና ምርቶችን በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማሠልጠንና የማደራጀት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ነው የገለጹት።

ከገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነው የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት ገበታውን ቦታው ላይ ላሉ ማህበረሰቦች በማጋራት ሀገርን በውብ በረከቱ ሊያጠግብ የምርቃቱን ቀን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል።

# ሆቴሎቹ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ገልጸዋል፡፡

ሆቴሉ ከዚህ ቀደም ከነበረው በተለየና በተሻለ ሁኔታ የኢትዮጵያን ባህል በሚገልጽ አቀባበል እንግዶችን ለማስተናገድ እየሠራ እንደሆነም አስታውቀዋል፡፡ በተቻለ መጠን ሆቴሎች በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል፤ የሚመጡ መሪዎች ደስተኛ ሆነው የሚሄዱበትንም አገልግሎት ማቅረብ አለባቸው ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

የግራንድ ፓላስ ሆቴል ተወካይ አቶ ኤልያስ ሙሉጌታ በበኩላቸው፤ መሰል ጉባዔዎች በሀገሪቱ መካሄዳቸው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሆቴሎች አቅም የሚፈተሽበት ነው ብለዋል፡፡ በዚህም በአዲስ አበባም ሆነ በተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች ያሉ ሆቴሎች ምን ያህል ውብ እንደሆኑ ለጎብኚዎች የምናስተዋውቅበት ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

ሆቴሎች የሚሰጡትን አገልግሎት በማስፋትና ጥራቱን የጠበቀ በማድረግ ሀገራቱን የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ ይኖርባቸዋል ያሉት አቶ ኤልያስ፤ 37ኛው የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔም የሆቴል ኢንዱስትሪውን አንድ ርምጃ የሚያራምድ ነው ብለዋል፡፡

ሆቴሉ ዘንድሮ የአፍሪካ ህብረት እንግዶችን ለመቀበል ሲዘጋጅ ሁለተኛው መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም እንግዶችን በባህላዊ አቀባበል ከማስተናገድ አንስቶ እያንዳንዱን እንግዳ ደህንነቱ በተጠበቀ መልኩ ለማስተናገድ ዝግጅቱን አጠናቋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ሂልተን ሆቴል ለዘንድሮ የአፍሪካ ህብረት የመሪዎች ጉባዔም የሆቴል ክፍሎችን ከማደስ አንስቶ በቂ ዝግጅት በማድረግ እንግዶችን ለመቀበል በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝ የገለጹት ደግሞ የሆቴሉ የሽያጭ ክፍል ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ገላው ናቸው፡፡

ሆቴሉ በተለየ ሁኔታ ኢትዮጵያን ከፍ የሚያደርግ እና የሀገሪቱን ባህል የሚያስዋውቅ መስተንግዶውን ለማቅረብ ተዘጋጅቷል ያሉት አቶ ዳንኤል፤ በተጨማሪም ለእንግዶች መረጃ የሚሰጥ እራሱን የቻለ የአገልግሎት ይኖረናል ብለዋል፡፡

መንግሥት በብዛት የሚስተዋለውን የመሠረተ ልማት ችግሮች በመቅረፍ እንግዶችን በጥሩ ሁኔታ ማስተናገድ የሚቻልበትን አማራጮች ማቅረብ ይኖርበታል ሲሉም አስታየታቸውን አጋርተዋል፡፡

# "የሀገራዊ ምክክርና የሽግግር ፍትህ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የሀገር ሽማግሌ ፕሮፌሰር አህመድ ዘካሪያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ከዚህ በፊት ሥልጣን ላይ ብቻ ያለው አካል እየተወያየ ውሳኔ የሚሰጥበትን ልማድ በመቀየር ህብረተሰቡ ውይይት አድርጎ የኢትዮጵያን ችግር ነቅሶ ለማውጣትና መፍትሄ ለማመላከት እድል የሚከፍት ነው፡፡

የምክክር ኮሚሽኑ ችግሮችን በመለየት እና የመፍትሄ ሃሳብ በማዋቀር ለሀገሪቷ ትልቅ የለውጥ አቅጣጫ የሚሰጥ ይሆናል ያሉት ፕሮፌሰር አህመድ፤ ከሀገራዊ ምክክሩ ጎን ለጎን የሽግግር ፍትህ መምጣቱ ደግሞ ለብዙ የሀገሪቱ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት የምክክሩን ውጤታማነት ያጎለብታል ብለዋል፡፡

የምክክር ኮሚሽኑ ሥራ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግሮችን ፣ መፍትሄዎች እና አቅጣጫዎች የመሰብሰብና እሱን የማደራጀት ነው ያሉት ፕሮፌሰር አህመድ፤ የሽግግር ፍትሁ ግን ይቅርታና ማካካሻን የሚያጠቃልል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሀገራዊ ምክክሩና የሽግግር ፍትሁ ተደጋግፈው መካሄዳቸውም ለብዙ የሀገሪቱ ችግሮች መፍትሄ የሚሰጥበት ይሆናል ብለው እንደሚያስቡ ፕሮፌሰር አህመድ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የሕዝቡ ጥያቄ በግለሰብ አልያም በተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ደረጃ ሲቀርብ ይደመጥ እንጂ የሕዝቡ ትክክለኛ ፍላጎት መለየት ባለመቻሉ ብዙ ችግሮች ተፈጥረዋል ያሉት ፕሮፌሰር አህመድ፤ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ካለፉት 50 ዓመታት ጀምሮ ያሉ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት ለሕዝቡ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሚሰጥበት ይሆናል ብለው እንደሚጠብቁ ገልጸዋል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ የሀገር ሽማግሌዎችን ጨምሮ ሁሉም ህብረተሰብ ክፍል የተውጣጡ አካላት እንዲሳተፉ መደረጉም ትክክለኛ መፍትሄ ላይ ለመድረስ ትልቅ ፋይዳ እንደሚኖረው አክለዋል፡፡

የሀገር ሽማግሌዎች የህብረተሰቡን ችግር በመፍታት አብሮነቱን በማስቀጠል አበርክቷቸው ትልቅ ነው ያሉ ሲሆን በሀገራዊ ምክክር ሂደት ውስጥም ሀገሪቷ ሰላም እንድትሆንና ችግሮች በሰላማዊ መንገድ እንድትፈታ ለማድረግ ጥረታቸውን ይቀጥላሉ ብለዋል፡፡

ፕሮፌሰር አህመድ ሀገራዊ ምክክሩና የሽግግር ፍትሁ ለሀገር ግንባታ ትልቅ መሣሪያዎች መሆናቸውን በመረዳት ህብረተሰቡ ለውጤታማነታቸው እንዲተባበር ጠይቀዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሌማት ትሩፋት ፕሮግራም የበለጠ ስኬታማ እንዲሆን

የለውጥ ኃይሉ ወደ ሥልጣን መምጣቱን ተከትሎ ተግባራዊ ካደረጋቸው ሀገራዊ የልማት ፕሮግራሞች መካከል አንዱ የሌማት ትሩፋት ነው። የፕሮግራሙ ዓላማ በዋናነት በሀገሪቱ የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በቤተሰብ ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ እና የአመጋገብ ሥርዓትን ማሻሻል ነው።

ከዚህም ባለፈ፤ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በመተካት የሥራ ዕድልን ከመፍጠር ጀምሮ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ ለማሳደግ የሚያስችል ዓላማ ሰንቆ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ሲሆን፤ ተስፋ ሰጪ ውጤት እየተመዘገበበት የሚገኝ ፕሮግራም ነው፡፡

ፕሮግራሙ በሀገር አቀፍ ደረጃ ችግር የሆነውን የሕፃናትን መቀንጨር መከላከል የሚያስችል፤ ዜጎች ባላቸው አቅም፣ በአነስተኛ ድጋፍ የተመጣጠነ ምግብ የሚያገኙበትን አስቻይ ሁኔታ የሚፈጥር ነው። እንደሀገር ያለንን ሥርዓተ ምግብ ጤናማ በማድረግ ሂደትም ጠቀሜታው የጎላ ነው።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ ዮሐንስ ግርማ (ዶ/ር) ሰሞኑን እንዳስታወቁት፣ በሌማት ትሩፋት መርሐ-ግብር በ2016 በጀት ዓመት አምስት ወራት አምስት ቢሊዮን 726 ሊትር ወተት፣ 328 ነጥብ ሁለት ሺህ ቶን ስጋ፣ 96 ነጥብ ሰባት ሺህ ቶን ማርና ከሶስት ቢሊዮን በላይ የእንቁላል ምርት ተገኝቷል።

በእነዚህ ወራትም 315 ሺህ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች ለተጠቃሚዎች ተሰራጭተዋል። የወተት ላም ዝርያ ማሻሻል፤ የተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያዎችን የማቅረብ ሥራም የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው።

የእንስሳትን ጤና አገልግሎት ከማሻሻል አኳያም የክትባት አገልግሎት ሽፋንን ለማሳደግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፤ የድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎችን ጨምሮ፣ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታን የመከላከል እና በበሽታው የተያዙ አዳዲስ አካባቢዎችን ከበሽታው የማፅዳት ሥራ ተሠርቷል፡፡

ሀገራችን ያሏትን ሀብቶች በአግባቡ መጠቀም ካልቻሉ ሀገራት በዋነኛነት ተጠቃሽ ስለመሆኗ በስፋት የሚነገር የአደባባይ ሚስጥር ነው፤ይህንን እውነት ለመቀልበስ በተለያዩ ወቅቶች የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ስኬታማ መሆን ሳይቻል ቀርቶ ከፍ ያለ የሀብት ብክነት ሲስተዋል ኖሯል።

ከዚህም የተነሳ እንደ ሀገር በብዙ ፈተናዎች አልፈናል። በምግብ እህል እራስን ያለመቻል እና የተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ችግሮች በብዙ ፈትነውናል። በዚህም ምክንያት አንገት በሚያስደፉና የሀገርን ክብር በሚፈታተኑ ክስተቶችን ለማለፍ ተገድደናል።

የድርቅ አደጋ በመጣ ቁጥር ለከፋ አደጋ ተጋላጭ መሆን፤ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ መግፋት፤ ከተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ጋር በተያያዘ ለተለያዩ በሽታዎች ተጋላጭ መሆን፣ ወዘተ እንደ ሀገር ብዙ ዋጋ ያስከፈሉን፣ ዛሬም እያስከፈሉን ያሉ የችግሩ ማሳያ ተደርገው የሚወሰዱ ፈተናዎቻችን ናቸው።

በእጃችን የነበሩትን /ዛሬም ያሉትን እነዚህን አቅሞች እና በጓሯችን ሊፈጠሩ የሚችሉ እድሎች በአግባቡ ማስተዋል፤ ለነሱ የሚሆን ስትራቴጂክ እይታ መፍጠር የሚያስችል ብቃት ያለው አመራር አለመኖር፤ የአቅሞቹና እድሎቹ ተጠቃሚዎች ሳንሆን ረጅም ዘመናትን እንድናሳልፍ ሆነናል።

ይህን የአመራር ክፍተት በማስወገድ የለውጡ መንግሥት እየሄደበት ያለው መንገድ ፣ በተለይም ሀገር በብዙ ችግሮች እየተፈተነች ባለበት አሁናዊ ሁኔታ ውስጥ ትርጉም ያለው ውጤት ማስመዝገቡ፤ የሚበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ትልቅ ሀገራዊ ስኬት ነው።

ፕሮግራሙ ሰፊው የገጠሩ ማህበረሰብ በቀላሉ ተጨማሪ ሀብት ማመንጨት የሚያስችለው ከመሆን ባለፈ፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገውን ከፍተኛ ፍልሰት በመከላከል፤ የገጠሩ ማህበረሰብ የተረጋጋ ሕይወት እንዲመራ የተሻለ እድል የሚፈጥር ነው። ወደ ውጪ የሚደረግ ስደትንም ሊቀንስ የሚያስችል ነው።

ከዚህ አንጻር ፕሮግራሙ የበለጠ ስኬታማ እንዲሆን የሚመለከታቸው አካላት፤ ተሞክሮዎችን ከማስፋት ጀምሮ፤ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በየጊዜው አግባብ ባለው መልኩ በመገምገም እና ዘላቂ መፍትሄዎችን በማስቀመጥ በትኩረት እና በቁርጠኝነት ሊንቀሳቀሱ ይገባል።

በተለይም በከተሞች አካባቢ የሚገኙ የፕሮግራሙ አስፈጻሚ አካላት፣ የፕሮግራሙን ዓላማ ከማስረጽ ጀምሮ ለተግባራዊነቱ የቢሮክራሲ ሰንሰለቶችን ማሳጠር፤ አስፈላጊ ድጋፎችን አግባብ ባለው መልኩ ማቅረብ፤ችግሮችም ሲያጋጥሙ ፈጥኖ በመንቀሳቀስ ለፕሮግራሙ ሁለንተናዊ ስኬት ከፍ ባለ የኃላፊነት መንፈስ ሊንቀሳቀሱ ይገባል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሠላም ለኪ

ግርማ መንግሥቴ

ብዙዎች እንደሚመሰክሩት፣ እኛም (ሌላው እንኳን ቢቀር) ደመነፍሳችን እንደሚነግረን፣ የሠላም ትክክለኛ ትርጉሙ የሚታወቀው እራሱ ሠላም የጠፋ እለትና እኛንም ሠላም የራቀን ቀን ነው። በቃ፣ ከዚህ በላይ የሠላምን ምንነት፣ ስለሠላም ፋይዳና ትርጓሜ የሚናገር የለም። "አለ" ከተባለም ያው የአካዳሚክስ ጉዳይ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም።

ወደ ወቅታዊው የሀገራች የሰላም ሁኔታና ይዞታ በቀጥታ ከመሄዴ በፊት ስለ "ሠላም" ጥቂት ልበል። መቼም የሰላም ጉዳይ ምን ያህል አንገብጋቢ፤ ምን ያህል የእለት ተእለት እንቅስቃሴያችንን እንደሚገዛው ለመገመት አይከብድም አይደለም ፤ የሰው ልጅ እጣ ፈንታም የቱን ያህል በሠላምና ሠላም ላይ እንደተደላደለ ለመረዳት ብዙም የሚቸግር አይደለም። በተጨባጭ አሁን ላይ እያየነውም ያለነውም ይሄንኑ ነው።

ከዛም ባለፈ እንደ ሀገር፣ የሠላም እጦትም እንበለው የሠላም መደፍረስ በዓለም አቀፍ የዲፕሎማሲም ሆነ ሌሎች እንቅስቃሴዎቻችን ላይም ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ፣ የሰሜኑን ጦርነት ተከትሎ በተጨባጭ የታየና ሀገርና ሕዝብን በብዙ መልኩ የተፈታተነ ነው። "ውሻ በቀደደው . . ." እንደሚባለው ክስተቱ ለታሪካዊ ጠላቶቻችን የጥፋት ሴራ እንደ አንድ እድል ሆኖ የታየበት ሁኔታም እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ።

አሁን ላይስ፣ "ሀገራችን ምን ላይ ነች?" ከተባለ፣ ተደጋግሞ ሲነገር እንደምንሰማው "አንጻራዊ ሰላም" ላይ ነች። የሰላሙ ደረጃ ምንም ይሁን ምን፣ አሁን ላይ ሀገሪቱ እንደ ሀገር ከነበረችበት የህልውና ስጋት ነጻ ነች። ለዚህ ደግሞ የተከፈለው መስዋእትነት ትልቅ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ መስዋእትነቱ ትልቅ እፎይታን ፈጥሯል።

በርግጥ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ዛሬም የሰላም ጥያቄ ዋነኛ ጥያቄ ነው። ከሰላም ጋር በተያያዘ በሕዝባችን ውስጥ ያለው ስጋት ገና ብዙ መሥራትን የሚጠይቅ ነው። አሁንም ዜጎች ወጥቶ ለመግባት ብዙ ፈተና አለባቸው። በተለይም በአማራ ክልል ካለው የሰላም እጦት ጋር በተያያዘ የክልሉ ሕዝብ የተደራረቡ ችግሮች ሰለባ እየሆነ ነው።

ይህ ጸሐፊ ሰሞኑን የዩኒቨርሲቲዎችን የተማሪዎች አቀባበል ለመመልከት ወደ ተወሰኑ ዩኒቨርሲቲዎች ጎራ በማለት፣ በተለይም ባለፉት ሁለት ዓመታት ጦርነት ከተደረገባቸው አካባቢዎች ከመጡ ተማሪዎች ጋር ለመወያየት ሞክሯል። ጦርነቶች ባይኖሩ እነዚህ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡት ከዛሬ ሶስትና አራት ዓመት በፊት እንደ ነበር በቁጭት ሲናገሩ ታዝቧል።

ቀደም ባለው ጊዜ የዩኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን ጀምረው ያቋረጡ ተማሪዎችም ያለ ትምህርት እቤታቸው ቁጭ ብለው ወራትን እያሳለፉ ነው፤ እነዚህ ተማሪዎች እንደ ብጤዎቻቸው ተምረው እንዳይመረቁ ያደረጋቸው የሠላም እጦቱ መሆኑን በተለያዩ መንገዶች ራሳቸው ሲናገሩ እየተሰማ ይገኛል። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ እንዳይመረቁ ብቻም ሳይሆን፣ የተሻለ ነገን እንዳያስቡ እንደሚያደርጋቸው ለማሰብ የሚከብድ አይሆንም።

የሠላም እጦቱ ያደረሰው ጉዳት ይህ ከላይ የጠቀስነው በተማሪዎቹ ላይ ያደረሰው ማህበራዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት ብቻ አይደለም፤ ኢኮኖሚውንም ሸንቁጦታል። የሰሞኑን፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር የመጀመሪያውን ሩብ በጀት ዓመት የተመለከተ ሪፖርት ያየ (ወይም፣ ያነበበ) ሰው የሀገራችን ሰላም መደፍረስ ኢኮኖሚያችንን ምን ያህል ወደ ኋላ እንደ ጎተተው በግልፅ ይመለከታል።

ሪፖርቱ ከጦርነትና ከግጭቶች የተነሳ ማግኘት እየቻልን ማግኘት ያልቻለውን፤ ያጣነው፣ ከእጃችን ያመለጠውን ሀብት ይመለከታል። "ሠላም ቢሆን ኖሮ ..." በማለትም ፀጉሩን ከመንጨትም አልፎ ከንፈሩን ሲነክስ ውሎ ከንፈሩን ሲነክስ ማደሩ የግድ ይሆናል። ችኩልና ስሜታዊ ከሆነም ራሱን ይዞ ሊጮህ ይችላል። እስከዚህ የሚደርስ ሀገራዊ ጉዳት አስተናግደናል።

በያዝነው ወር የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት "በሀገሪቱ በተለያዩ አካባቢዎች በሚታዩ ግጭቶችና የፀጥታ ችግሮች ምክንያት፣ ሀገራዊ ይዘት ያለው ጥናት ማካሄድ አለመቻሉን ዋና ዳይሬክተሩ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ አስታውቀዋል። ይህም ፣ ከጦርነት ይልቅ ሠላም መሻሉን፤ ሠላም ባለመኖሩ ምክንያት እየሆነ ያለውን፤ በተለይም ከላይ በጠቀስናቸው ወሳኝ ተቋማትና ሌሎችም ላይ እያደረሰ ያለውን ምስቅልቅሎሽ ያመላከተ ነው። አሁንም ምርጫችን ሠላም መሆን እንዳለበት፤ ባስቸኳይ ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ መምጣት ያለብን መሆኑን የሚጠቁም ነው። እዚህ ላይ የሠላም እጦት በገቢ ላይ ያደረሰውን አደጋ አነሳን እንጂ እራሱ ግጭቱ እየበላው ያለውን፣ የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ከዚሁ ጋር አክለን እንየው ብንል ስሌቱ የቱን ያህል የከፋ እንደሚሆን ማሰብ አይከብድም፤ በችግሮቻችን ላይ የከፋ ተጨማሪ ችግር ይዞ ስለመምጣቱ ሁለቴ ማሰብ የሚጠይቅ አይሆንም ።

> **አሁንም ምርጫችን ሠላም መሆን እንዳለበት፤ ባስቸኳይ ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ መምጣት ያለብን መሆኑን የሚጠቁም ነው።**

ከሁሉም በላይ በየሥፍራው ንፁህ ሕይወታቸውን እያጡ ያሉት ዜጎች፣ ረሀብ እየቀጣቸው ያሉት ወገኖች፣ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ... ወዘተ ሲታሰቡ አሁኑኑ ለሰላም በር አለመክፈት ማለት በእነዚህ ሁሉ ላይ መጨከን ነውና ጉዳዩ ጊዜ የሚሰጥ አይደለም።

አሁን ጥያቄው "ምን ይደረግ?"፣ "ምን እናድርግ?" የሚል እንደሚሆን ለማንም ግልፅ ነው። መደረግ ያለበት ከላይ እንዳልነው ከተዘፈቅንበት ጦርነት መውጣት፤ ጨክኖ ምርጫን ሠላም እና ሠላም ላይ ብቻ በማድረግ ለሕዝብ ሠላም እና ደህንነት መሥራት ነው።

ነፍሳቸውን ይማረውና ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ተለይተው የሚታወቁባቸው በርካታ አገላለፆች ያሏቸው ሲሆን፤ አንዱም "ደህና ሁን ጠብመንጃ" የሚለው ነው። ፕሮፌሰሩ የዋዛ ሰው እንዳልነበሩ የሚታወቅ ነው። በመሆናቸውም ዝም ብለው "ደህና ሁን ጠብመንጃ" እንደማይሉም የታወቀ ነው።

በሌላ መንገድ "ጠመንጃ ነካሽ አለ" እያሉን ነው። በቀላሉ ከጠመንጃ ነካሽነት ተላቅቆ ጠብመንጃን "ደህና ሁን" የሚል ሰው እንደማይኖር እየነገሩን ነበር። እንዳሉትም ሰውየው "ደህና ሁን ጠብመንጃ"ን በአደባባይ ከለቀቁት ከ25 ዓመታት በላይ ቢያልፍም ትንቢት ይመስል ይኸው እስካሁን ደፍሮ፣ ለሀገርና ለወገኑ ብሎ "ደህና ሁን ጠብመንጃ" ያለ አልተገኘም።

ስለ ሠላም ብሎ፣ ለሠላም ተገዝቶ . . . ለሠላም እጁን የሰጠ አልተገኘም። የጠረጴዛ ዙሪያ ውይይትን የደፈረ ወፍ የለም። ይባስ ብሎ ነገር አለሙ ሁሉ "ጠብንጃ ፈርስት!!" እየሆነ ያለ ይመስላል። ከፕሮፌሰሩ "ደህና ሁን ጠብመንጃ" ወዲህ እጅግ የከፋ ጦርነት አካሂደናል። አሁንስ አይበቃንም???።

አትዮጵያ፣ ሠላም ለኪ!!! (ሰላም ላንቺ ይሁን!!!)

# ነፃ ሃሳብ

# ለፀረ-ሙስና ትግሉ ውጤታማነት፣ ምሕረት የለሽ ተጠያቂነትን ማስፈን ይገባል!

**ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ**

ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ጽሑፍ ሳነብ፣ ጽሑፉ ውስጥ እንዲህ የሚል ሃሳብ ተመለከትኩ። ‹‹... ሙስና በኢትዮጵያ የየዕለት ሕይወት አካል ሆኗል...›› ... በእርግጥ ሃሳቡ ሙስና በሀገሪቱ ውስጥ የደረሰበትን ደረጃ ቀላልና ግልጽ በሆነ (አስደንጋጭ ቢሆንም) አገላለፅ ለማሳየት ጥሩ እድል ይፈጥራል፡፡ ይህ ሃሳብ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የሙስና ወንጀል ለመግለፅ ቢያንስ እንጂ አይበዛም፡፡

ኢትዮጵያን እግር ከወርች ይዘው ጉዞዋን የኋልዮሽ ካደረጉባት አስከፊ ችግሮች መካከል አንዱ ሙስና ነው፡፡ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ‹‹በሙስና ውስጥ አለመሳተፍ እና ሙስናን መዋጋት ወንጀል ነው›› የተባለ እስኪመስል ድረስ የወንጀሉ ተሳታፊ ለመሆን የሚደረገው እሽቅድድም እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን ነው፡፡ በጉቦ፣ በምዝበራ፣ በማጭበርበርና በሌሎች የሙስና መልኮች የሚፈፀመው የወንጀል ብዛትና ዓይነት ታይቶም ተቆጥሮም አያልቅም፡፡ ጉዳይ ለማስፈጸም ጉቦ መጠየቅና መስጠት ‹‹በሕግ ያልተፃፈ ግዴታ›› ሆኗል፡፡ የሚጠየቀውና የሚከፈለው የጉቦ መጠን ደግሞ ‹‹ጆሮ አይስማ›› ያሰኛል፡፡

ቀደም ሲል በረቀቀ መንገድ ሲፈፀም የነበረው ሙስና አሁን በማን አለብኝነትና በግላጭ ይደረጋል። ያለጉቦና ዝምድና አገልግሎት ማግኘት ፈፅሞ የማይታሰብ እየሆነ ነው፡፡ በአጠቃላይ ዜጎች ጉዳይ የማስፈጸምና አገልግሎት የማግኘት መብት እንዳላቸው እንዲሁም የመንግሥት ሹማምንትና ሠራተኞች ደግሞ የዜጎችን አገልግሎት የማግኘት መብት የመፈፀምና የማስፈፀም ግዴታ ያለባቸው መሆኑ ጨርሶ ተዘንግቷል፡፡ ‹‹ሌብነትን እየተለማመድነው ይሆን?›› ብሎ የመጠየቂያው ትክክለኛ ጊዜ ላይ ሳንሆን አንቀርም፡፡

በኢትዮጵያ ያለውን የሙስና ወንጀል የከፋና አስፈሪ የሚያደርገው ደግሞ ሙስና ከብሔር ፖለቲካ ጋር ተጋምዶ ሲፈፀም መቆየቱና አሁንም ተባብሶ መቀጠሉ ነው፡፡ የጎሳ መዛመድን መነሻ ያደረገ ጥልፍልፍ የሙስና ወንጀል በእጅጉ ተንሰራፍቷል። ይህም በአንድ በኩል ሙስናን ተፀይፈው የሚሠሩ ጥቂት ሐቀኛ ሠራተኞችን፣ በሌላ በኩል ወንጀሉ ያሰባሰባቸው ጎሳ አባል ያልሆኑትን ለማጥቃት ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ደግሞ ሙስና ከጉቦ፣ ከማጭበርበርና ከዝርፊያ የተሻገረ ትርጉምና ውጤት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ይህ ዓይነቱ አካሄድ ገንዘብ በማባከንና ጉቦ በመቀበል የሚቆም ሳይሆን እጅግ አስከፊ ወንጀሎች እንዲበራከቱ በማድረግ ሀገር እንዳትጠገን ሆና እንድትፈራርስ የሚያደርግ አደገኛ መመዘዝን ያስከትላል፡፡

እንዲህ የተንሰራፋውን የሙስና ተግባር ለመቀነስ በየጊዜው ልዩ ልዩ ጥረቶች ቢደረጉም፣ ሙስናን ትርጉም ባለው መጠን መቀነስ ያስቻለ ተጨባጭ ለውጥ ሊመዘገብ ግን አልቻለም፡፡ ከዓመት በፊት ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ መቋቋሙ ይታወሳል። የመንግሥትን ሙሉ አቅም በመጠቀም በተቀናጀና በተናበበ ሁኔታ ሙስና የፈጠረውን ችግር ለመቀልበስ እንደተሰየመ የተነገረለት ኮሚቴው ሰባት አባላት ያሉት ሲሆን፣ መንግሥት በሙስና ላይ የሚያደርገውን ዘመቻ የማስተባበር፣ በጥናት ተለይተው ከቀረቡት በተጨማሪ ሌሎችንም ተዋንያን የመለየትና ለሕግ እንዲቀርቡ የማድረግ ኃላፊነት እንዳለው ተገልፆ ነበር።

በፀረ-ሙስና ዘመቻው የአገሪቱ የጸጥታ እና የፍትሕ ዘርፍ እንዲሁም የመንግሥት የመሬት አስተዳደር ቅድሚያ እንደተሰጣቸው እንዲሁም የመንግሥት ቤቶች አስተዳደር፣ የፋይናንስ፣ የመንግሥት ገቢ እና ጉምሩክ ሥርዓት፣ የአገልግሎት አሰጣጥ፣ አስተዳደር እና የመንግሥት ግዢን የመሳሰሉ ዘርፎች ከፍተኛ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል ከተባሉት መካከል እንደሚገኙ ተገልጿል፡፡ በፍትሕ እና በፀጥታ ዘርፍ ሥልጣናቸውን ያለ አግባብ በመጠቀም የዜጎችን ሰላም እና የሀገርን ደህንነት የማስጠበቅ ኃላፊነታቸውን ተገን አድርገው በተለያዩ ሕገ-ወጥ መንገዶች ከግለሰቦች እና ከንግድ ድርጅቶች ገንዘብ እና ሀብት ለመውሰድ የተንቀሳቀሱ ተጠርጣሪዎች ተለይተዋል ተብሎ መነገሩም የሚታወስ ነው፡፡

ሙስናን ለመዋጋት ተብሎ ኮሚቴ ሲቋቋም ይህ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚህ ቀደምም መሰል ኮሚቴዎች ተቋቁመው እንደነበር ይታወሳል፡፡ ‹‹በሙስና ላይ ዘመቻ ተከፈተ›› ተብሎ ይወራና ሕዝቡም ‹‹ሙሰኛው ሁሉ ተጠራርጎ ለፍርድ ሊቀርብ ነው›› ብሎ በፀረ ሙስና ዘመቻው ላይ መጠነኛ ተስፋ ሲያደርግ ይስተዋል ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ተደጋግሞ ተደርጎ የዘመቻው ውጤት ግን ከዜሮ ያልተሻለ ሆኖ ሲገኝ፣ ሕዝቡም ተሰላችቶ ዘመቻውን ‹‹ጉራ ብቻ›› ብሎ ሲገልፀው ነበር፡፡ ‹‹ቀደም ሲል የተቋቋሙ የፀረ ሙስና ኮሚቴዎችስ የት ደረሱ? ምን ተግባራትንስ አከናወኑ?›› ተብሎ ቢጠየቅ አጥጋቢ ምላሽ ማግኘት አዳጋች ነው፡፡

በእርግጥ ብዙ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በፀረ-ሙስና ዘመቻው በሙስና ወንጀል ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2016 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ድረስ ሙስናን ለመከላከል በተሠራ የቅድመ መከላከል ሥራ፣ ከዘጠኝ ቢሊዮን ብር በላይ ከምዝበራ ማዳን እንደተቻለ የፌዴራል ሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮሚሽን አስታውቋል፡፡ ከ829 ሚሊዮን ብር በላይ በሙስና የተገኘ ገንዘብም ተመላሽ ሆኗል፤ ከአንድ ኪሎ ግራይ በላይ ወርቅ ወደ መንግሥት ካዝና እንዲገባ ተደርጓል፤ ከአራት ሚሊዮን ካሬ ሜትር በላይ መሬት ከምዝበራ ማዳን ተችሏል፡፡

‹‹ለመሆኑ የዘመቻ ተግባር ለሙስና ችግር ዘላቂ መፍትሔ ይሆናል?›› ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ የፀረ ሙስና ዘመቻ ሙስናን ትርጉም ባለው መልኩ ለመቀነስና ከስሩ ለመንቀል ዘላቂና አስተማማኝ መፍትሔ አይሆንም! ‹‹የሀገር የደኅንነት ሥጋት ሆኗል›› የተባለ ችግር ሐቀኛና ዘላቂ በሆነ ስር ነቀል መዋቅራዊ ለውጥ እንጂ በአንድ ሰሞን ዘመቻ መፍትሔ አያገኝም። ሙስና መንግሥታዊ ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰባዊ መገለጫም እየሆነ ነው፡፡ ‹‹ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል›› በሚል ብሂል የሚኖርና ሐቅንና መርሕን ተከትሎ ሥራን የሚሠራን ሰው ‹‹ሞኝ፣ ጅል›› ብሎ የሚያሸማቅቅ ኅብረተሰብም ሆነ በሥርዓትና በመዋቅር ታግዞ የሚዘርፍና የሚያጭበረብር ሹመኛና ሠራተኛ በዘመቻ አይደነግጥም፡፡

ዘመቻውን እያካሄድኩ ነው የሚለው መንግሥትም ሙስናን ለመዋጋት ከልቡ ቁርጠኛ ሊሆን ይገባል፡፡ ስር ለሰደደ ችግር የአንድ ሰሞን ዘመቻን መፍትሔ አድርጎ መመልከት፣ በሙስና ላይ የመዝመት ፅኑ ፍላጎትን አያሳይም፡፡ ስለሆነም ለሐቀኛና ዘላቂ መፍትሔ ዝግጁ በመሆን ዘመቻው ከአንጀት መሆኑን ማሳየት ይገባል፡፡ አለበለዚያ ግን ነገሩ ሁሉ ከአንጀት (የእውነት) ሳይሆን ከአንገት (የይምሰል) እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

ሙስና በኢትዮጵያ ላይ ያስከተለውና እየፈጠረ የሚገኘው ቀውስ በቃላት ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ችግሩ በአጭር ጊዜ ከሚታይ የአገልግሎት አሰጣጥ ብልሽት እስከ ትውልድ መምከንና ሀገር መፍረስ የሚደርስ አሰቃቂ ቀውስን የሚያስከትል አደጋ ሆኗል፡፡ ኅብረተሰቡ በተቋማት ላይ ያለው እምነት እንዲሸረሸር በማድረግ በመንግሥት ተስፋ ይቆርጣል። ከዚህ ባሻገርም ሙስና ሞራልንና ሥርዓትን በገንዘብና በዝምድና በመተካት ማኅበረሰባዊ መስተጋብርና መተማመን እንዲዳከም በማድረግ የሀገር መፍረስን ያስከትላል፡፡

ሀገራት ሙስናን ለመታገል የተለያዩ የአሠራር ሞዴሎችን ይተገብራሉ፡፡ አንዳንድ ሀገራት ሙስናን በመከላከል ላይ ብቻ የሚያተኩር ሥርዓት (Corruption Prevention Model) ሲዘረጉ፣ ሌሎች ደግሞ የሕግ ማስከበር ትኩረት የሚሰጥ አሠራር (Law Enforcement Model) ይተገብራሉ፡፡ መከላከልን እና ሕግ ማስከበርን ያጣመረ ሥርዓትን (Multi-Purpose Anti-Corruption Model/The Universal Model/) የሚተገብሩ ሀገራትም አሉ፡፡

> **በተለያዩ ጊዜያት ተጀምረው የነበሩት የፀረ ሙስና ትግሎች የተኮላሹት መንግሥታት በሚፈለገው ልክ ድጋፍና እገዛ ባለማድረጋቸው ነው። ስለሆነም ለፀረ ሙስና ትግሉ ጠንካራ መንግሥታዊ የድጋፍ ሥርዓት በመፍጠር ምሕረት የለሽ ተጠያቂነትን ማስፈን ይገባል**

የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮችን ለመቅረፍ በየተቋማቱ ያሉ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች በተቋሞቻቸው ውስጥ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት የሚስችል የአሠራር ሥርዓት ጥናት እንዲያካሂዱ የሚያስችላቸውን የሥራ ነፃነትና አቅም መፍጠር እንደሚያስፈልግ የፌደራል የሥነ-ምግባር ፀረ-ሙስና ኮሚሽን የጥናት ምክረ ሃሳቦች ይጠቁማሉ፡፡ መሰል የአሠራር ሥርዓት ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ተከስተው ከፍተኛ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ለችግሩ መንስኤ የሚሆኑ ሁኔታዎችን መርምሮ በማውጣት የመፍትሔ ሀሳቦችን በማቅረብ ችግሮች ከወዲሁ እንዳይከሰቱ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ግልጽ የሆነ የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት የሚፈጠሩ የሙስናና ብልሹ አሠራር ችግሮች በቀላሉ እንዲጋለጡ ለማድረግ ያግዛል፤ የሥነ-ምግባር ትምህርትና ሌሎች የመከላከል ሥራዎች የሚያተኩሩባቸውን የሥራ አካባቢዎች ለመወሰን በማስቻልም ረገድ ዕገዛ ያደርጋል፡፡ ይህ የአሠራር ጥናት ለሙስናና ብልሹ አሠራር የሚዳርጉ የአሠራር ክፍተቶችን እንዲለይ እና የታዩ ክፍተቶችን ለመፍታት የሚያግዙ የማሻሻያ/የመፍትሔ ሃሳቦችን እንዲጠቁም ይጠበቃል፡፡

የመንግሥት ንብረትና ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን፣ ተገልጋዮች እንዲጉላሉ፣ ለሥነምግባር ተቃራኒ የሆነ ድርጊትን ወይም ባሕርይን የሚያበረታታ ወይም እንዳይፈጸሙ የማይከላከል፣ ለብልሹ አሠራር የተጋለጠ፣ የአሠራር ሥርዓትን በፅናትና በሐቀኛነት መታገል ያስፈልጋል፡፡ ሁሉንም የሙስና ስጋቶች በአንድ ጊዜ ለመቅረፍ አዳጋች በመሆኑ የሙስና ተጋላጭነት ደረጃን እና ሙስና ቢፈፀም ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቀዳሚ/ከፍተኛ ተብለው የሚገመቱትን በመለየት የፀረ-ሙስና ዘመቻውን ማካሄድ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ሙስናን ለመከላከል የተተገበሩ አሠራሮች በቂ ውጤት እንዳላስገኙ በመገንዘብ ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫዎችን ከመስጠት ጀምሮ ጠንካራ የሕግ ማስከበር እርምጃዎችን መውሰድ ይገባል፡፡ የፀረ ሙስና ትግሉ በትክክለኛ ቁመና ላይ እንደሚገኝ ማረጋገጫ ከሚሆኑ መለኪያዎች መካከል አንዱ ጠንካራ፣ ነፃና በሕዝብ ተቀባይነት ያለው የፀረ ሙስና ተቋማት አደረጃጀት መፍጠር ነው፡፡ ስለሆነም የፀረ-ሙስና ትግሉ ከመንግሥትም ሆነ ከገዢው ፓርቲ ተፅዕኖ በተላቀቀና ጠንካራ መሠረት ባለው ነፃና ገለልተኛ ተቋም ሊመራ ይገባል፤ ተቋሙ ለፀረ-ሙስና ዘመቻው ቁርጠኛ በሆኑ ሀገር ወዳድ ባለሙያዎች እንዲመራና እንዲዋቀር መደገፍም ያስፈልጋል። የሙስና መከላከልና የሕግ ማስከበር ሥራዎችን በተለያዩ ተቋማት ማከናወን የፀረ ሙስና ትግሉ የተበታተነ እንዲሆን በማድረግ ትግሉ እንዲዳከም ስለሚያደርግ፣ የፀረ-ሙስና ተቋማት አደረጃጀቶች ለትግሉ ውጤታማነት አመቺ ሊሆኑ ይገባል፡፡

‹‹ሙስና ጠላታችን ነው›› ብሎ ከመናገር አልፎ ድርጊቱን በተግባር ለማሸነፍ የሚያበቃ ቁመና መላበስ ያስፈልጋል፡፡ እስካሁን የነበረውንና አሁንም ያለውን የፀረ ሙስና ሥርዓትና አደረጃጀት ጉድለቶች በአግባቡ ፈትሾ የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ ተገቢ ነው፡፡ የሙስና አስተሳሰብንና ድርጊትን የሚጠየፍ ኅብረተሰብና መንግሥት መፍጠር ካልተቻለ፤ ጠንካራና የተረጋጋ አገር፣ መንግሥትና ኅብረተሰብ ለመፍጠር ያለው ዕድል በጣም ጠባብ ነው፡፡

የፀረ ሙስና ትግሉን በዋናነት እንዲያስተባብሩ ኃላፊነት የተሰጣቸው ተቋማት ጠንካራና ተከታታይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ፣ የመደጋገፍ እንዲሁም በፀረ ሙስና ትግሉ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመለየት የሚያስችል የተቀናጀ አካሄድ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሙስናን የመዋጋት ትግሉ ለጥቂት ተቋማት ብቻ የሚተው ተግባር ባለመሆኑ ሁሉም ዜጋ የፀረ ሙስና ትግሉን በዋናነት እንዲያስተባብሩ ኃላፊነት ለተሰጣቸው ተቋማት ዘርፈ ብዙ ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

በተለያዩ ጊዜያት ተጀምረው የነበሩት የፀረ ሙስና ትግሎች የተኮላሹት መንግሥታት በሚፈለገው ልክ ድጋፍና እገዛ ባለማድረጋቸው ነው፡፡ ስለሆነም ለፀረ ሙስና ትግሉ ጠንካራ መንግሥታዊ የድጋፍ ሥርዓት በመፍጠር ምሕረት የለሽ ተጠያቂነትን ማስፈን ይገባል፡፡

የትምህርት ተቋማትን፣ መገናኛ ብዙኃንን፣ የሃይማኖት ተቋማትን፣ መደበኛ ያልሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ ኅብረተሰቡ ሠርቶ መበልፀግን ብቻ አማራጭና ባሕል እንዲያደርግ እንዲሁም የፀረ-ሙስና ትግሉ ባለቤትና ዋና ተዋናይ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ የፖለቲካ ቁርጠኛነት ያስፈልጋል፡፡ ከሁሉም በላይ፣ ሙስና የሀገር ሕልውና አደጋ እንደሆነ ሊታወቅና፣ ለፀረ-ሙስና ዘመቻው ሊሰጥ የሚገባው ትኩረት ይህን መራራ እውነት የሚመጥን ሊሆን ይገባል!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# ጊዜውን ለመዋጀት ፍጥነትን የሚጠይቀው የሰው ሠራሽ አስተውሎት

ወርቅነሽ ደምሰው

አሁን ባለንበት «ዘመነ ቴክኖሎጂ » የረቀቀ የሰው ሠራሽ አስተውሎት (Artificial intelligence) በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል፤ ይህም የሰው ልጆችን ሥራ እያቀለለው ነው:: በተለይ ያደጉት ሀገራት ይህን ሰው ሠራሽ አስተውሎት በብዙ መልኩ በመጠቀም ወደ ተራቀቀ የቴክኖሎጂ ደረጃ እየደረሱ ይገኛሉ:: ይህ ሁኔታ ያለ ቴክኖሎጂ መኖር ቀላል እንዳይደለ ያመላክታል:: ታዳጊ ሀገራትም ይህንን ቴክኖሎጂ በፍጥነት በመተግበር ዓለምን የሚቀላቀሉበት መላ መዘየድ ይጠበቅባቸዋል::

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ የሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርተፊሻል ኢንተለጀንስ) እንደ እሳቤ የተጀመረው እ.ኤ.አ በ1950ዎቹ ገደማ ነው:: ሰው ሠራሽ አስተውሎት (አርተፊሻል ኢንተለጀንስ) የሚለውን ስያሜ የያዘው ግን እ.ኤ.አ 1955 መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ቴክኖሎጂው እያደገ መጥቶ አሁን ዓለምን ከሰው ሠራሽ አስተውሎት እሳቤ ውጭ ከማትሆንበት ደረጃ ላይ አድርሷታል:: በመሆኑም አሁን ላይ ነገሮች ያለሰው ሰራሽ አስተውሎት አስቸጋሪና አዳጋች የሚሆኑበት ጊዜ ላይ ደርሳለች:: የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ የሰው ሠራሽ አስተውሎት የዓለምን ኢኮኖሚ በስፋት እያንቀሳቀሰ ይገኛል:: እ.ኤ.አ 2022 ሦስት ነጥብ አንድ ትሪሊዮን ዶላር ሀብት እያንቀሳቀሰ ሲሆን፣ በቀጣይ 2025 ደግሞ እስከ አምስት ትሪሊዮን ዶላር ሀብት ሊያንቀሳቅስ ይችላል ተብሎ ተገምቷል::

**በዚህ ልክ የዓለምን ኢኮኖሚ እያንቀሳቀሰ የሚገኘውን ሰው ሠራሽ አስተውሎት ምንድነው፣ ለምን አገልግሎት ይውላል፤ እንዴትስ መጠቀም ይገባል?**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኃላፊ በአካል ግዛቸው (ዶ/ር) ሰው ሠራሽ አስተውሎት ስንል በተፈጥሮ የሰው ነው የሚባለውን አስተውሎት ለማሽን መስጠት ማለት እንደሆነ ይናገራሉ:: እሳቸው እንደሚሉት፤ እንደ ስልክ፣ ኮምፒዩተር፣ ኤሌክትሮኒክ የሆኑ መሣሪያዎች (እያንዳንዱ ኤሌክትሮኒክ መገልገያዎች) እና ለየትኛውም ኤሌክትሮኒክስ ማሽን ይህንን አስተውሎት መስጠት ማለት ነው:: ሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ማድረግ ከሚችላቸው ነገሮች ቋንቋን ይማራል፣ ብዙ ትምህርቶችን ያውቃል፤ እርምጃዎችና ውሳኔዎችን ይወስዳል:: ይህንን አስተውሎት ለማሽን ሰጠን ማለት በሰው የሚሠሩ ሥራዎችን በማሽን እንዲሠሩ ማድረግ ይቻላል:: በተለይ አንዳንድ ከሰው አቅም በላይ የሆኑት ሥራዎች ማሽኑ እንዲሠራ ማስቻል ነው ::

ማሽኑ የሚሰጠውን እውቀት ተጠቅሞ ውሳኔ መስጠት ላይ አስፈላጊ እርምጃዎች እንደሚወስድ ጠቅሰው፤ ጠቀሜታውም ምርትና ምርታማነት ለመጨመር እና አንዳንድ ሥራዎች ለማቀላጠፍ የሚረዳ ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ ይገልጻሉ::

ሰው ሠራሽ አስተውሎት ለሀገር እድገት የሚኖረው አስተዋፅዖ ከፍተኛ ስለሆነ ያደጉ ሀገራት ብዙ የሚጠቀሙበት ነው የሚሉት በአካል (ዶ/ር)፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን በግብርና፣ በትምህርት፣ በጤና እና በመሳሰሉት በርካታ ዘርፎች ላይ መጠቀም የሚቻል መሆኑን ጠቅሰው፤ እንዲያውም የማንጠቀምበት ዘርፍ የለም ማለት ይቻላል ይላሉ:: ለምሳሌም ወንጀልን ቀድሞ የመከላከል እና የመተንበይ ሥራዎችን ቀድሞ ሊሠራ ይችላል:: የተፈጥሮ አደጋዎችን መተንበይና ቅድመ መከላከል ላይ ዝግጅት እንዲደረግ ለማወቅ ያስችላል:: በግብርናው ረገድ በምን አይነት መሬት ላይ ምን አይነት እህል ብንዘራ የተሻለ ምርታማ መሆን እንችላለን ለሚለው ጥያቄ መረጃዎችን ሰብስቦ የሚያሳውቅ ነው:: የመሬቱን ለምነት ከምን ያህል ጊዜ በኋላ ነው ሙሉ ለሙሉ ሊጠፋ የሚችለው ቀጥሎ ምን ቢደረግ የተሻለ ሊሆን ይችላል የሚሉ እና የመሳሰሉ በርካታ ማወቅ የምንፈልጋቸውን ነገሮች ቀድሞ ማወቅ ያስችላል::

በቱሪዝም ኢንዱስትሪውም እንዲሁ አንድ ጎብኚ ለመጎብኘት ከመነሳቱ በፊት ካለው አቅም ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የትኛውን ቦታ ቢጎበኝ የተሻለ እንደሚሆን ለማወቅ ከፈለገ መረጃ ሊሰጠው እንደሚችል ይገልጻሉ:: እንዲሁም በኢትዮጵያ ቢዝነስ ለመክፈት ለሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት ዝርዝርና ጥልቀት ያለው መረጃ የሚሰጥ እንደሆነ ያብራራሉ::



በአካል ግዛቸው (ዶ/ር)



አቶ ዳንኤል ጌታቸው

እስካሁን ብዙዎቹ የሰው ሠራሽ አስተውሎት ሲስተሞች የተሠሩት በውጭ አገር ቋንቋዎች ስለሆነ ሀገራችንን ተጠቃሚ አላደረገም:: ስለዚህ በሀገራዊ ቋንቋዎች ላይ መሠራት አለበት ይላሉ:: እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ላይ የተጀመሩ ሥራዎች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ በአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስትቲዩት በኩል የተሠራ ድምፅን ወደ ጽሑፍ የሚቀይር ሲስተም አለ:: ይህም በአማርኛ እና በአፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች የተሠራ ሲሆን ሌሎቹን በሀገሪቱ ያሉ ቋንቋዎች ለማካተት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ይገኛሉ።: እነዚህ ሥራዎች ለሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ልክ መሠረት የመጣል ያህል እንደሆነም ያስረዳሉ::

አሁን ያለው ቋንቋዎችን የመጠቀም ያለበት ደረጃ ከሌሎች ሀገራት አንጻር ሲታይ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች መጠቀም በጣም አነስተኛ ነው:: ብዙ ቴክኖሎጂ ቢኖሩም ብዙዎች ደግሞ ሊጠቀሙበት አይችሉም። በተለይ በገጠር ያሉ ያልተማሩ ሰዎች ቀላል ስላልሆነ አይጠቀሙበትም። አሁን ያሉትን በማሳደግ ቋንቋዎች ላይ በመሥራት ተጠቃሚነት ማስፋት ያስፈልጋል::

«አሁን ያለንበት ዘመን የዳታ (የመረጃ ዘመን) ነው። ዳታ ነዳጅ ነው ይባላል:: ዓለምን እያንቀሳቀስ ያለው ዳታ ነው:: ከዳታ ብዙ ነገሮችን እንማራለን:: ስለዚህ ከሰው ሠራሽ አስተውሎት መራቅ አይቻልም፤ ከራቅን ደግሞ በጣም እንጎዳለን» የሚሉት በአካል (ዶ/ር) ግብርናው ላይ ባይሠራ የሚባክን ብዙ ነገር መኖሩን ይጠቅሳሉ። በትራንስፖርት፣ በአደጋ መከላከል፣ በምርጫ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በሰው ሠራሽ አስተውሎት ሊደገፉ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ሐሰተኛ መረጃ እና የጥላቻ ንግግሮችን ለማጣራት የምንችልባቸው በርካታ መንገዶች ሰው ሠራሽ አስተውሎት ላይ መሠረት ያደረጉ ናቸው ሲሉ አብራርተዋል::

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ አሁን ላይ ከዓለም ወደኋላ ላለመቅረት ቴክኖሎጂን መያዝ ያስፈልጋል:: ዓለምን እየመሩ ያሉት የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ናቸው። ተራማጅ ሀሳቦች እያራመዱ ወደፊት መጓዝ አስፈላጊ ይሆናል:: «ቆየት ብለን መጀመራችንን እንደተጎዳ ብቻ ማየት የለብንም:: እኛ ዓለም የደረሰበት ለመድረስ አሁን ላይ ያሉት የታረሙ ቴክኖሎጂዎች ይዘን ወደኛ ዓውድ እየቀየርን መጠቀም እንችላለን:: በጥሩ ሁኔታና አመራር በሁሉም ዘርፍ ቢሠራ ያዋጣል ብዬ አስባለሁ» ብለዋል::

በሰው ሠራሽ አስተውሎት ላይ የሚነሱ ብዙ ስጋቶች አሉ ያሉት በአካል (ዶ/ር)፤ ከእነዚህ ውስጥ አንደኛው ስጋት አውቶሜሽን ስለሆነ ሁሉንም ነገር ማሽን ከሠራው ሰዎችን ሥራ ያሳጣል የሚል እንደሆነ ገልጸዋል:: እሳቸው እንዳሉት፤ ስጋቱ እንዳለ ሆኖ ማሽኑ ደግሞ ተከታታይነት፣ ቀልጣፋነትና ምርታማነት የሚጨመር እንደሆነ ይታወቃል:: ሺ ሰው ከሚሠራው ይልቅ ማሽኑን ተጠቅሞ አምስት ሰው እየሠራው የአሥር ሺ እና ከዚያ በላይ ሰው ያህል የበለጠ ምርት ማምጣት ያስችላል::

ምርታማነቱን በአሥር እጥፍ ሲያሳድገው የሚያመጣው ገቢም በዚያ ልክ በጣም ይጨምራል ማለት ነው:: «እንደ ኢትዮጵያ ስናይ በእኔ እምነት የትኛውን ሥራ የሚያስብል ነው፤ ለብዙዎቹ ሥራዎች አነስተኛ ክፍያ የሚከፈልባቸው ናቸው:: ይህንን ማድረግ ይሻላል ወይስ ማክሮ ኢኮኖሚው ላይ የሚገኘውን ዘጠኝ እጥፍ ጥቅም ጨምረን ለእነዚህ ሰዎች የተሻለ የሥራ እድል እንፍጠር በሚል የሚታሰብ ሊሆን ይችላል» ሲሉ አስረድተዋል::

ሌላኛው ሰው ሠራሽ አስተውሎት ላይ የሚነሳው ስጋት ማሽኑ አንዳንድ ውሳኔዎች ቢሳሳትስ የሚል ነው ሲሉም በአካል (ዶ/ር) ይጠቅሳሉ፤ በአሜሪካ «ኮምፓስ» የተሰኘው ሶፍት ዌር በፍርድ ቤት ተግባራዊ ሆኖ እንደነበር አስታወሰው፤ ሶፍት ዌሩ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ የተደረጉት ጥናቶች የሰጠው ውሳኔ የተሳሳተ መሆኑን ማመላከታቸውን በአብነት ያነሳሉ::

ይህ መሳሳት የሚመጣው ከሚሰጠው ዳታ እንደሆነ የገለጹት በአካል (ዶ/ር)፤ አሁን ላይ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን እንዴት ኃላፊነት የሚሰማው ማድረግ ይቻላል የሚለው ላይ መታሰብ እንዳለበት አመላክተዋል። እሳት ላይ ስጋት አለ ብለን መጠቀም እስካልተውን ድረስ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን ጥንቃቄ በተሞላው መልኩ መጠቀም እንደሚገባ አስገንዝበዋል::

የሰው ሠራሽ አስተውሎት የአገራችንን ሉዓላዊነት በማስከበር ረገድ የሳይበር ደህንነትን ለመጠበቅ፣ የአቪዬሽንን ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ፣ ምርታማነትን ለመጨመር፣ ገበያን ለማስፋት እና ለመሳሰሉት ሥራዎች በእጅጉ አስፈላጊ መሆናቸውን በአካል (ዶ/ር) አመልክተዋል:: የሰው ሠራሽ አስተውሎት ምሕዳሩ ላይ በአፍሪካ በተለይ በደቡብ አፍሪካ የሚታየው ተነሳሽነት እና በኢትዮጵያ ኢንስቲትዩት በማቋቋም እየተከናወነ ያለው ተግባር መነሳሳትና መነቃቃትን መፍጠሩን ጠቅሰው፣ ይህም ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ተናግረዋል::

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የሰው ሠራሽ አስተውሎትና ሮቦቲክስ የፒ ኤች ዲ ተመራማሪ አቶ ዳንኤል ጌታቸው የበኩላቸው የበአካልን (ዶ/ር) ሀሳብ በመጋራት የሰው ሠራሽ አስተውሎት አዲስ ነገር አለመሆኑን ይናገራሉ:: ሰው ሰራሽ አስተውሎት እንደ ኢትዮጵያ ገና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት በብዙዎች ዘንድ እንደ ቅንጦት ሲታይ መቆየቱን ጠቅሰው፣ በእነዚህ ሀገሮች ጥቅሙ ብዙም እንደማይታወቅ ይጠቁማሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ በደንብ ባይታወቅም በሰው ሠራሽ አስተውሎት ሲስተሞችን በመቆጣጠር ብዙ አገልግሎት እየሰጡ የቆዩ እንደ ቴሌ ኮሙዩኒኬሽን እና ባንክ ያሉ ተቋማት እንዳሉ ይጠቅሳሉ::

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ አብዛኞቹ ዘርፎች ላይ ሊሠራባቸው የሚችሉ ቢሆንም እንደ ሌሎቹ ሀገራት በብዙ ሥራዎች ላይ እየተጠቀምን ነው ለማለት ይቸግራል ይላሉ:: የአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ ዳንኤል፤ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሆኑ ቋንቋዎችን ዲጂታላይዝ ማድረግ እና የመሳሰሉትን ጠቅሰው፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎትን ወደ ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎች በማምጣት ሁሉንም ማኅበረሰብ አካታች የሚያደርጉ ሥራዎች መሥራት እንደሚያስፈልግ አቶ ዳንኤል ጠቁመዋል::

እሳቸው እንደሚሉት፤ ሰው ሠራሽ አስተውሎት በደንብ አውቆት ከህሎቱ ኖሮት የሚሠራ ሰው (ማኅበረሰብ) ይፈልጋል:: ስለዚህ ግንዛቤ ሊያሰፉ የሚችል ተከታታይነት ያላቸው ሥልጠናዎች መስጠት ያስፈልጋል:: በተለይ ለሰዎች አድካሚና ብዙ ወጪ የሚያስወጡ ጉዳዮችን ማቃለል ይቻላል:: ለምሳሌ አንድ ወንጀለኛ ወንጀል ሠርቶ በካሜራ ታይቶ የሚፈለግ ቢሆን በሰው ፈልጎ ማግኘት በጣም አታካች ነው:: ሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ግን ባለው መረጃ መሠረት ተናብቦ የመሥራት ሲስተም አማካኝነት በቀላሉ ወንጀለኛውን ሊይዘው ይችላል:: ወንጀለኞችን በፍጥነት በመለየት የሰውን ድካም ማቅለል የሚችል ነው ብለዋል::

ሰው ሠራሽ አስተውሎት በትክክለኛ መንገድ ለትክክለኛ ዓላማ ጥቅም ላይ ከዋለ በተገቢው ፍጥነት ከተሠራበት ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ አንዳንድ ጊዜ ዘግይቶ መቀላቀል ጥሩ የሚሆንበት ሌሎች የሄዱበት መንገድ በማየት ብዙ ወጪ ሳይወጣ በቀላሉ የተሻለ ቴክኖሎጂ ገዝቶ ለመጠቀም ያስችላል:: ነገር ግን በዚያው ልክ በፍጥነት አለመጠቀም ሌላ ኪሳራ እንደሆነ አስረድተዋል::

ሰው ሠራሽ አስተውሎት እንደኛ ሀገር ብዙ ሥራዎች ይፈልጋል የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ በዘርፉ የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት እና ብዙ ሥራዎች የሚሠሩ ተቋማት ማብዛት የመጀመሪያ ሥራ መሆኑንም ጠቁመዋል:: የሚሠራው ሳይኖር ተግባሩ ላይ ትኩረት ቢደረግ ብዙ ጥያቄዎች የሚያስነሳ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ከሆነ ደግሞ ከውጭ ሲስተሞች ሳንላቀቅ ጥገኛ ሆኖ ለመቅረት እንደሚዳርግ ሲገልጹ፤ «የእኛን ነባራዊ ሁኔታ የሚረዳ የተማረ ሰው ማብዛት እና ለባሕልና እምነት ቅርብ የሆኑ ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል፤ ያ ካልሆነ ነገሮች ሊጋጩና እኛ ባላሰብነው መንገድ ሊያሄዱ ይቻላሉ» በማለት ነው። ለዚህም ኢትዮጵያዊ ሁሉን አካታች የሆኑ ዳታዎች የሚሰበሰብ የሚተነትን ባለሙያ ያስፈልጋል በማለት አስረድተዋል::

አሁን ያለው በተቋም ደረጃ መቋቋሙ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት የሚያሳይ ነው ያሉት አቶ ዳንኤል፤ በዩኒቨርሲቲዎች እየተሰጡ ያሉ ትምህርቶች ዝግጅቶችም መነቃቃት እየተፈጠረ ለመሆኑ አንድ ማሳያ ብለዋል:: ይህንን በማስፋት ረገድ አስፈላጊ ከሆኑ ዘርፎች በመጀመር የግል ዘርፉን በማሳተፍ የአኗኗር ዘይቤ ማስተካከል የሚችሉ አዳዲስ ሲስተሞች ሊሠሩ ይገባል ነው ያሉት::

በሰው ሰራሽ ዘርፍ ላይ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ዘርፎች ላይ በተለያየ መልኩ ሥራዎችን የሚያሻሽሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ሲመጡ እንደ ስጋት የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች እንዳሉም ያመለክታሉ:: ሰው ሠራሽ አስተውሎት በሐሰት የተፈበረኩ መረጃዎች ለመሥራት በጣም አመቺ መሣሪያ እየሆነ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ማኅበራዊ ሚዲያው ላይ የሚለቀቁ መረጃዎች ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የማይገናኙ ሲሆን፤ እነዚህ መረጃዎች በተለይ በአፍሪካ ሀገሮች ለፖለቲካ አለመረጋጋት ስጋት የሚያመጡ ሲሆን፤ አደጋው ከፍተኛ የሚሆነው ይህንን መሣሪያ ለዚህ ዓላማ የሚጠቀሙ ሰዎች እየበዙ ከመጡ እንደሆነም አመላክተዋል::

ከሥራ ማጣት ጋር ተያይዞ ያለውን ስጋት አስመልክቶም ባለን ነገር ላይ ከቆየን ነው ሥራ ማጣት የሚመጣው ያሉት አቶ ዳንኤል፤ «በሰው ሠራሽ አስተውሎቱ ምናልባት በሲስተሞች የሚተኩ ሥራዎች እየበዙ ሊሄዱ ይችሉ ይሆናል:: ነገር ግን በሌላ በኩል ደግሞ አዳዲስ ሥራዎችም ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ማሰብ ያስፈልጋልና ዛሬ ላይ አሳሳቢ ነገር ላይ አይደለምና መሥራት መድረስ ያለብን ነገር ላይ መድረስ አለብን» ሲሉ ተናግረዋል::

አሁን ላይ ሀገራት የሰው ሠራሽ አስተውሎት ላይ አሜሪካና ቻይና የመሳሰሉ ሀገራት እያበለጸጓቸው ያሉ ትልልቅ ሲስተሞች መኖራቸው ጠቁመው፤ እነርሱ በሚሠሩት ሲስተም የሚመጣ ጥፋት ካለ የመጀመሪያ ተጠቂዎችና ተጎጂ የሚሆኑት በሲስተሙ ደካማ የሆኑ አገራት እንደሆኑ ይናገራሉ:: «በመሆኑም እኛም የእነሱ ሲስተም እየተጠቀምን መቀጠል የለብንም በራሳችን መሥራት አለብን» ሲሉ አቶ ዳንኤል ሀሳባቸው አጠቃለዋል::

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የባሕር በር ጉዳይ - ከዓለም አቀፍ ሕግ አኳያ

**እስቴር ኤልያስ**

የባሕር በር የሌላት ትልቋ ሀገር ኢትዮጵያ፣ ዛሬም እንዳለፉት በርካታ ዓመታት ሁሉ የወደብ አገልግሎትን ለማግኘት ጥገኛ ሆና ቀጥላለች፡፡ ይህ አካሄዷ መዳረሻው ፖለቲካዊም ኢኮኖሚያዊም ክስረት እንደሆነ የተገነዘቡት ጠቅላይ ሚኒስትሯ ከወራት በፊት የባሕር በር ተጠቃሚ መሆን በሚያስችል ጉዳይ ላይ እንወያይ ሲሉ ሐሳቡን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሲመከሩ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ የባሕር በር ባለቤት የመሆን እንቅስቃሴዋን የጀመረችው በሐሳብ ደረጃ ሲሆን፣ ይህ ሐሳብ እየጎለበተ መጥቶ በተለይ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት በማነቃቃት ላይ ይገኛል። ብዙዎችም ለተቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንዛቤው እንዲኖረው በማድረግ ላይ በመሆናቸው ጥቂት የማይባለው የኅብረተሰብ ክፍል በጉዳዩ እየተሳበበት መምጣቱም እሙን ነው፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ከ200 በላይ ከሚሆኑ ሀገራት መካከል የባሕር በር ከሌላቸው 44 ሀገራት መካከል አንዷ ናት፤ ይሁንና ሰፊ እና ታላቅ ሀገር እንደሆነች ግልጽ ነው፡፡ ከወደብ ጥገኝነቷ ለመላቀቅ እና ለራሷም ሆነ ለቀጣናው የሚጠቅም ጠንካራ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ደግሞ የባሕር በር ግድ እንደሚላት የታወቀ ጉዳይ ሆኗል፡፡ እንዲያም ሆኖ የባሕር በርን ለማግኘት ቅድሚያ የምትሰጠው በሀገር ውስጥ በጉዳዩ ዙሪያ ከመወያየትና ከመነጋገር ባለፈ ከሀገራት ጋርም መነጋገርንና መስማማትን እንደሆነም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲነገር ቆይቷል፡፡ የባሕር በርን ለማግኘት ስትል ምንም አይነት ጠብ አጫሪነትን እንደማትፈጽምም ተደጋግሞ ተወስቷል፡፡

ኢትዮጵያ ሰፊ የባሕር በር ባለቤት የነበረች ሀገር እንደመሆኗ ሁሉ ዛሬም የባሕር በር ባለቤት ለመሆን ትሻለች፡፡ አገልግሎቱን ለማግኘት አካሄዷ ምን መሆን አለበት? በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የወጣ ኮንቬንሽንስ የኢትዮጵያ የባሕር በር እና የወደብ ጥያቄ ከሕግ አኳያ ሲታይ ምን ይላል? ስንል የዘርፉን ምሑራን አነጋግረናል፡፡

የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤ ከፍተኛ የሕገ መንግስት ተመራማሪ የሆኑት አቶ ዓምደገብርዔል አድማሱ እንደሚሉት፤ ከባሕር በር ጋር በተያያዘ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያፀደቀው ዋንኛ የዓለም አገራት የሚተዳደሩበት የባሕር ሕግ አለ፤ ይህ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለ እና ከዚያ ጀምሮ ብዙ ችግሮችን መፍታት የቻለ ሕግ ነው። ይህ ሕግ ስለአፍሪካም መግቢያው አካባቢ ተንትኖ ያስቀመጠ ነው፡፡

የባሕር በር የሌላቸው ሀገራትን በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የባሕር ሕግ የሚያስቀምጠው ድንጋጌ አለ፤ በተለይም በአንቀጽ 69 ላይ ከንዑስ ቁጥር አንድ እስከ አምስት ባለው ላይ እንዲሁም አንቀጽ 25 እና አንቀጽ 125 ላይ በመሠረታዊነት የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት እንዴት አድርገው ጎረቤቶቻቸው ካሉ እና የባሕር በር ካላቸው ሀገራት ጋር መጠቀም እንዳለባቸው የሚያስረዳ መሆኑን አቶ ዓምደገብርዔል ይናገራሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ እነዚህ አንቀጾች የባሕር በር በሌለው እና ባለው ማለትም በሁለቱ አገራት በሚደረግ ስምምነት መሠረት የባሕር በር እንዲጠቀሙ መንገድ የሚያስቀምጡ ናቸው፡፡ ከአንዳንድ ጉዳዮች በስተቀር ሁሉንም አገልግሎት እንዲያገኙ የሚገልጽ ሐሳብም የያዙ ናቸው፡፡

የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት እቃቸውን ከማጓጓዝ አልፎ ከባሕሩ የሚገኘውንም በረከት መቋደስ የሚችሉ መሆናቸውን ሕጉ ያስቀምጣል ሲሉ የተናገሩት ከፍተኛ የሕገ መንግሥት ተመራማሪው፣ ለአብነት የዓሣ ምርት የመጠቀምንም መብት ያጎናጽፋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪው ያዕቆብ አርሳኖ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ያለፈው መንግሥት ወደብን የሚያክል ታላቅ ሀብት አሳልፎ የሰጠው ጉዳይ መሆኑን ያስታውሳል። ይህን ከእጅ የወጣን ታላቅ የሆነው የባሕር በርን ማግኘት ቀላል እንዳልሆነ ጠቅሰው፤ ጠንካራ ሥራ የሚጠይቅ ትልቅ ጉዳይ ነው ብለዋል። የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ ትልቋን ኢትዮጵያ የሚያክል ሥራ የሚጠይቅ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ አንድ የባሕር በር የሌለው አገር የባሕር በር የመጠቀም መብት አለው፤ መብቱ ግን ከጎረቤቱ ጋር በመግባባት እና በስምምነት ላይ የተመሠረተ መሆንን የሚጠይቅ ነው፡፡ ለሁሉም ስምምነት እና ውይይት የግድ ይላል፡፡ ከሀገራቱ ጋር አብሮ በመጠቀም ለማደግ መልካም ግንኙነት መፍጠርን ይጠይቃል፡፡

ያዕቆብ (ዶ/ር)፣ ልክ እንደ አቶ ዓምደገብርዔል ሁሉ ኢትዮጵያን የባሕር በር ተጠቃሚ ሊያደርጓት የሚችሉ አንኳር ጉዳዮች አንዱ ትልቅ ሀገር መሆኗ ነው ይላሉ። በተለይም ኢትዮጵያ ትልቅ ኢኮኖሚ የምታንቀሳቅስ ሀገር እንደመሆኗ የባሕር በር በማጣት እንዲህ አይነት ጫና ውስጥ መግባት የሌለባት ሀገር እንደሆነችም ያስረዳሉ። ስለዚህም የባሕር በርን ሕጉም በሚፈቅደው ሁኔታ በስምምነት መጠቀም ተመራጭ የሆነ አካሄድ ነው ሲሉ የአቶ ዓምደገብርዔል ሐሳብ ያጠናክራሉ፡፡

ስለዚህም ይላሉ የውሃ ጉዳይ ተመራማሪው ያዕቆብ (ዶ/ር)፣ የባሕር በርን ለማግኘት ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ መጠቀም ወሳኝ ነው፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የባሕር በር ተጠቃሚ የነበረች ብትሆንም አሳልፋ ለኤርትራ የሰጠች መሆኗ የሚታወቅ ነው፤ ይህን ደግሞ "መልሼ እወስዳለሁ" ማለት አይቻልም ሲሉ ጠቅሰው፤ ይህን ለማድረግ ሕጉም አይፈቅድም በማለት ይናገራሉ፡፡ በስምምነት ግን የሚሆን በመሆኑ ከወዲያኛውም ሀገር የሚፈልገው ጉዳይ ታውቆ በውይይትና በስምምነት የባሕር በር ተጠቃሚ መሆን እንደሚቻል ያመለክታሉ፡፡

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ ይህ ስኬታማ ይሆን ዘንድ የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የፐብሊክ ዲፕሎማሲን መጠቀም አንዱ ጉዳይ ነው፡፡ የተለያዩ ኮንፈረንሶችን መጠቀምም ሌላው ተጠቃሽ አካሄድ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በቂ ጥናት እና ለድርድር የሚሆን ዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል። በቂ ትኩረትም ተሰጥቶት አስፈላጊ ከሆነ ኮሚሽንም ተቋቁሞለት ቢሠራ ኢትዮጵያ ተጠቃሚነቷን ከፍ እያደረገች ልትሄድ ትችላለች፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የወጣ ኮንቬንሽንም በስምምነት መሆኑን ያዛል፡፡ ኢትዮጵያ በሌላ ሀገር ወደብ ስትጠቀም የዚያን የምትጠቀምበትን ሀገር ደህንነት ጠብቃ ፍላጎትን አሟልታ ነው፡፡ ይህ በስምምነት የሚቋጭ ጉዳይ ነው፡፡ በስምምነቱ ውስጥ ደግሞ ቁጥጥር አለ፡፡

ጂቡቲ በወደብ ከምታገኘው 70 በመቶ ያህል ሀብቷን የምትሰበስበው ከኢትዮጵያ እንደሆነ የሚገልጹት ተመራማሪው፣ እንዲያም ሆኖ ኢትዮጵያ የምትፈልገውን ሁሉ በፈለጋት ጊዜ ማስገባት እንደማትችል አስታውሰዋል። በዚህ ውስጥ ሆና አጣዳፊና ድንገታዊ ጉዳይ ቢያጋጥማት እንኳ የምትፈልገውን ነገር በፈለገችበት ጊዜ ማስገባት እንደማትችል ሁሉ ደብቃ የሚጠቅማትን እቃ ማምጣትም አይሆንላትም ብለዋል፡፡ ልታስገባ ለፈለገችው እቃ ለማስገባት የቱንም ያህል አቅም ቢኖራት እንኳ አቅሟም ሆነ ፍላጎቷ የተገደበ መሆኑ የሚታወቅ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

እንደ ከፍተኛ የሕገ መንግሥት ተመራማሪ አቶ ዓምደገብርዔል ገለጻ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ካሉ ከ200 በላይ ሀገራት አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት በርካታ ሲሆኑ፣ በላቲን አሜሪካ ውስጥ የምትገኝ የባሕር በር የሌላት ሀገር የሆነችው አንዷ ቦሊቪያ ናት፡፡ ሌሎች በመደራደር ማለትም ሰጥቶ በመቀበል ሕግ የባሕር በር ያገኙ ናቸው፡፡

ሌላው አፍሪካ ውስጥ ደግሞ ኮንጎ ኪንሻሳ ከኮንጎ ብራዛቪል እና ከአንጎላ የባሕር በር የማግኘት እድል አግኝታለች፡፡

ልክ እንደ የውሃ ተመራማሪው ያዕቆብ (ዶ/ር) ሁሉ በዓለማችን የባሕር በር ከሌላቸው እና ትልቅ ሀገር ከሚባለት ውስጥ አንዷ ኢትዮጵያ ናት የሚሉት አቶ ዓምደገብርዔል፣ የባሕር በር አለመኖር ለብዙ የኢኮኖሚ ችግር የሚዳርግ ጉዳይ ነው ይላል፡፡

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ በሁለት ምክንያት የባሕር በር የመጠየቅ መብት እንዳላት ይታያቸዋል፡፡ ከአሰብ ወደብ ጋር በተያያዘ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ወስደው ጣሊያኖች ቅኝ ግዛት ሲገዙ ስምምነቶች ነበሩ፡፡ እነዛ ስምምነቶች በራሳቸው በጣሊያኖች የተጣሱ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን ለሁለተኛ ጊዜ መጥተው ሲወሩ ስምምነቱን ጥሰዋል፡፡ ያ ስምምነት ኢትዮጵያን የሚጎዳ ነው፡፡

በተጨማሪም ኤርትራ ከኢትዮጵያ የወጣችበት መንገድ ቅቡልነት ያለው አይደለም፡፡ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የባሕር በር የነበራት ሀገር ሆና ቆይታለች፡፡ በቅኝ ግዛት ምክንያትና በሌሎችም ምክንያቶች የነበራት ወደብ እንድታጣ ተደርጓል፡፡ በአሁኑ ወቅት ግን የባሕር በር ጥያቄ የመጠየቅ መብቷ በዓለም አቀፍ ሕግጋት የተጠበቁ እንደሆነ ይታያል፡፡

ይሁንና የባሕር በርን ለማግኘት የዓለም አቀፉ ሕግ የሚያስቀምጠውን ድንጋጌ መከተል ወሳኝ ነው። አንደኛው ጉዳይ ድርድር ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሰጥቶ መቀበል የሚባለው መርሕ ነው፡፡ ጂቡቲም ሆነች ኤርትራ እንደሚታወቀው ትልልቅ የሚባሉ ወንዞች የሏቸውም፡፡ የጥሪት እጥረት አለባቸው፡፡ መሬታቸውም የዚያን ያህል ለእርሻ አመቺ አይደለም፡ ፡ በመሆኑም ይህን መሠረት በማድረግ በሰጥቶ መቀበል መርሕ ኢትዮጵያ ከእነዚህ ሀገራት ጋር መነጋገር ትችላለች፡፡

ያዕቆብ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የባሕር በር ሊሰጡን የሚችሉ ሀገራት ለሕዝባቸውና ለሀገራቸውም ልማት ከኢትዮጵያ የሚፈልጉት ብዙ ነገር ስላለ እኛ ሳንሆን እነሱም ፍላጎታቸውን እያቀረቡ ስምምነት ላይ መድረስ የሚቻል ይሆናል ይላሉ፡፡ በእርግጥ ጥያቄው ከትልልቅ ነገር ሊጀመር ይችላል ሲሉ ተናግረው፤ ለአብነትም ሰጥቶ በመቀበል መርሕ ሊሆን እንደሚችል የአቶ ዓምደገብርዔልን ሐሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ መሬት ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰው፤ ከዚያም ያለፈ ነገር ሊጠየቅ እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡

የውሃ ጉዳይ ተመራማሪው፣ የራሳችን የሆነውን የዓባይ ወንዝ ላይ የሕዳሴ ግድብን ለመገንባት እንኳ የወሰደብን ጊዜ በጣም ብዙ ነው፡፡ ከመንግሥታት ጋር መከራከሩ፣ ያልገባቸውን ማስተማሩ፣ የሚሰነዘሩ ብሽሽቆችን መቋቋሙ እና ሌላ ሌላም ጫናን መጋፈጡ የወሰደው ሰፊ ጊዜ ነው፡፡ ይህ በሕዳሴ ግድብ ላይ የተወሰደው ጠንከር ያለ ሒደት ለአፍሪካ ቀርቶ ለሌላው ዓለም ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ተሞክሮ ነው።

እንዲያም ሆኖ የሕዳሴ ግድቡና የባሕር በሩን አንድ የሚያደርጉ አንዳንድ ሰዎች አሉ ያሉት ያዕቆብ (ዶ/ር)፣ ይህ ግን ትክክል አይደለም፡፡ ዓባይ ወንዝ የራሳችን ሀብት ሆኖ ስንጋፈጥ የነበረው አትጠቀሙም ከሚሉ አካላት ጋር ነበር ብለዋል፡፡

አሁን ግን የጎረቤት ሀገር ሆኖ ወደብን አትጠቀሙ ማለት አይቻልም፤ ሕጉ እንደሚያስረዳው ስላጠቃቀሙ መነጋገርን ነው እንጂ በፍጹም አይቻልም የሚለውን አይደለም ይላሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ጥያቄያችንን ውጤታማ ይሆን ዘንድ ክብደታችንን እዛ ላይ መጫን ይኖርብናል።

ስለዚህ ዓባይና የባሕር በር ልዩነት ያለው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዓባይን ለመገንባት የታየ የሁሉም ቁርጠኝነት ለባሕር በር ጥያቄው ስኬትም ሊደገም የሚገባው መሆን አለበት፡፡ ልክ የሕዳሴ ግድቡን ያለምንም ጦርነት ሰላማዊ በሆነ የዲፕሎማሲ ቋንቋ እዚህ ማድረስ እንደተቻለ ሁሉ የባሕር በሩ ጥያቄም በዚህ አግባብ ምላሽ እንዲያገኝ በቁርጠኝነት መሥራትን ይጠይቃል ብለዋል፡፡ ልዩነቱ ዓባይ የገዛ ንብረታችን በመሆኑ ልናዝበት የምንችለው መሆኑ ሲሆን፣ ያኛው ግን የሰው እንደመሆኑ ልናዝበት ሳይሆን በስምምነት እና በውይይት ማምጣት የምንችለው መሆኑ ነው፡፡

የዓለም ከአስር በመቶ በላይ ንግድ የሚዘዋወርበት ቦታ ቀይ ባሕር ነው የሚሉት ከፍተኛ ተመራማሪው፣ ከዚህ ጎን ለጎን በአሁኑ ወቅት በብዙዎች እይታ ውስጥ ያለ ስትራቴጂክ ሆኗል ይላሉ፡፡ በቀይ ባሕር ዙሪያ ካሉ ሀገራት በተጨማሪ በርቀት ያሉ ሌሎች ሀገራት እንደ ቻይና፣ አሜሪካ፣ ራሽያ፣ ቱሪክ እና መሰል ሀገራት ምን እያደረጉ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ሆኗል፡፡ በቀይ ባሕር ኮሪደር ውስጥ እነ ሳዑዲ ዓረቢያና የመንም በጣም ትልልቅ ወደብ ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ በሰጥቶ መቀበል ሕግ እና በዓለም አቀፍ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የወደብ ኮሪደር የማግኘት መብት እንዳላት ያሳያል ብለዋል፡፡

ልክ እንደ ያዕቆብ (ዶ/ር) ሁሉ እርሳቸውም ከሁሉም ነገር በላይ የሚያስፈልገው ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ነው ይላሉ፡፡ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆኑ አዋጭ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ እንደሚታወቀው ታሪካዊ ሀገር ናት፡፡ ነገር ግን ትልቁ ችግር በሀገር ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እምብዛም አለመኖሩ ተደማጭነትን ለማግኘት አሊያም ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲዊ ላይ ከፍ ብሎ ለመታየት የሚደረገውን አቅም ሲያዳክምብን ይስተዋላል ሲሉ ያመለክታሉ፡፡

ይህ በመሆኑ እኔ በበኩሌ ቅድሚያ ቢሰጠው ብዬ የምለው የሀገር ውስጥ ሰላም ላይ በጣም መሥራት ይጠበቅብናል የሚለው ላይ ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ ያንን በአግባቡ ከሠራን ኢትዮጵያ በሕዝብ ብዛት ከናይጀሪያ ቀጥላ በአፍሪካ ሁለተኛዋ ሀገር ናት፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን በጣም ትልቅ ኢኮኖሚ የምታንቀሳቅስ አገር ናት። ጂዲፒዋ (አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እድገቷ) በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህም በላይ የሦስት ሺ ዓመት ታሪክ ያላት ትልቅ እና ቀደም ሲል ከ100 እና 150 ዓመታት በፊት የምታስተዳድራቸው ወደቦችም የነበሯት ሀገር ናት። እነዚህንና ሌሎችንም እውነታዎችን በመያዝ የባሕር በርን የመጠየቅና የመደራደር መብቷ የተጠበቀ ነው፡፡ ትችላለችም ብለዋል፡፡

ስለዚህ የባሕር በርን እስከወዲያኛው ማጣት ፈተናው በሀገራችን ላይ በጣም ከፍ ያለ የኢኮኖሚ ጫና ያመጣል፡፡ እስካሁን በጂቡቲ የምንጠቀመው ወደብ የኪራይ ነው፡፡ የኪራዩ ክፍያ በጣም ከፍ ያለ ሲሆን፣ በቀን እየተከፈለ ያለው ዶላር ነው፡፡ ኢትዮጵያ አምራች የሰው ኃይል ያለባት ሀገር ሆና የባሕር በር ስለሌላት ብቻ ትልቅ ተጽዕኖ የሚያሳድርባት መሆኑ ይታወቃል በማለት አብራርተዋል፡፡

ከዚህ ባሻገር ወደብ አለመኖሩ ገቢ እና ወጪ ምርቷን ያወሳስበዋል፡፡ የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚም በተፈለገው ልክ እንዳያድግ ጫና ያሳድራል፡፡ ሀገራችን ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ያላት ሀገር ስለሆነች ተገቢው ኢኮኖሚ የማይኖር ከሆነ ዜጎቿ ምርጫቸውን ስደት ላይ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ የኢትዮጵያ ዜጎች መሰደዳቸው ጉዳቱ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የሚሰደዱባቸው ሀገራትም ጭምር ነው፡፡ ምክንያት ቢባል በሀገራችን ያለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ደካማ የሚሆን ከሆነ ወጣቱ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መሰደድን ምርጫው ስለሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በመዳረሻ ሀገራትም ላይ ጫና ይፈጥራል፡፡

ስለሆነም በሕዝብ ብዛቷ፣ በታሪካዊት ሀገርነቷ እና በአፍሪካ ደረጃ ያላት የጂዲፒዋ ጠንካራ መሆን ከግምት ውስጥ ገብቶ የባሕር በር ሊኖራት የሚገባት ሀገር መሆኗ የማይታበል ሐቅ ነው ብለዋል፡፡


ምሑራኑ እንደሚሉት፤ የሕግ ጉዳይ ከተነሳ ኢትዮጵያ አሰብን ያጣችበት መንገድ ፍትሐዊ እና ተገቢ ያልሆነ ነው፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ኢትዮጵያ ሀገሪቱን መልቀቅ የነበረባት የወደብ ተጠቃሚነቷን አስጠብቃ መሆን ነበረበት፡፡


ኢትዮጵያ አሁን እያነሳች ላለችው የባሕር በር ጉዳይ የዓለም አቀፉ ሕግ የሚያስቀምጠው አንኳር ጉዳይ ቢኖር በሀገራት መካከል በሚደረግ ስምምነት የሚወሰን መሆኑን ምሑራኑ ያመለክታሉ፡፡ ወደብ ካላቸው ሀገራት ጋር በሚደረግ ስምምነት የሚደረግ መግባባት እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ ይህም ስምምነት እንደየሀገሮቹ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል ሲሉ ጠቅሰው፤ ይህም መሬት ከመጠየቅ እስከ ትልልቅ ተቋማትን እስከመጋራት ሊደርስ እንደሚችል አመልክተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዲፕሎማሲውን የበለጠ ጠንካራ እንዲሆን ማድረግ ይጠበቃል ብለዋል።

ትልቅ ሀገር እንደመሆናችን ከእኛ ጋር ሊስማሙ ለሚችሉ ሀገራትም የሚስገኘው ጥቅም ትልቅ እንደሚሆን የሚታወቅ እንደሆነ ጠቁመው፤ ይህን ሳይረዱና ሳይፈቅዱ ቀርተው ለዘመናት የሚሸሹ ከሆነ የእኛ ችግር የሚያመጣው ፈተና የእነርሱም ፈተና መሆኑን ማሰብ መቻል አለባቸው ሲሉ አሳስበዋል፡፡


ማህበራዊ

# ሴቶች


ወይዘሮ አስካለ ደጉ


ወይዘሮ እመቤት አዱኛ


ወይዘሮ የሺእመቤት ሰለሞን


ወይዘሮ ጅሩ በዳዳ

## የገጠሯን ሴት ጫና ያቃለለው የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ

**ስምስም መንግሥቱ**

በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ወልመራ ወረዳ አንደኛ በርፌታ(በርፌታ ቶኮፋ) ቀበሌ ውስጥ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ጎረቤታሞች በሀገር ባሕል ልብስ ደምቀዋል። ምክንያታቸው ደግሞ ቀኑ ለእነርሱ የተለየ ስለነበር፤ ደስታቸውን ለመግለፅ አስበው ነው፡፡ ቀኑ ለማገዶ የሚሆን የከብት እዳሪ በመጠፍጠፍ ልስላሴውን አጥቶ የነበረውን እጃቸውን ከጉዳት የሚመልስላቸው ቴክኖሎጂን ማግኘት የቻሉበት ነው፡፡

ቀደም ሲል የሚጠቀሙት የማገዶ ቴክኖሎጂ ጭስ የሰውነትና የልብሳቸውን ጠረን የሚቀየር ብቻ ሳይሆን፤ ለዓይን ሕመምና ለሌላም የጤና ችግር በማጋለጥ ያስከትልባቸው የነበረው ችግር ቀላል አልነበረም፡፡ አዲሱ ቴክኖሎጂ እነዚህን ችግሮች የሚያስወግድላቸው እና በአጠቃላይ የማጀታቸውን ሥራ የሚያቀልላቸው በመሆኑ የተለየ የደስታ ስሜት ፈጥሮላቸዋል፡፡

በዕለተ ዓርብ በቀበሌው ተገኝተን የአካባቢውን ሴቶች ደስታ ስንጋራ እንደገለፁልን፤ የመንደሩ ሴቶች የባዮጋዝ ተጠቃሚ ከሆኑ ገና አንድና ሁለት ወራቸው ነው፡፡ በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ እፎይታ ማግኘታቸውን ይናገራሉ፡፡ ለማገዶ የሚሆን ኩበት ለማግኘት የከብት እዳሪን አጠራቅሞ መጠፍጠፍና የእንጨት ማገዶ ለቅሞ ማዘጋጀት የዘወትር ሥራቸው ነበር፡፡ ከአባወራውና ከልጆች በፊት ከእንቅልፍ ማልዶ በመነሳት እሳት አያይዞ ምግብ ማዘጋጀት የሴቷ ኃላፊነት በመሆኑ በዚህ መልኩ ሴቶቹ በየቀኑ ይደክማሉ። አሁን ግን ባዮጋዝ ተጠቃሚ መሆናቸው ድካማቸውን አቅልሎላቸዋል፡፡

እኛም በስፍራው በተገኘንበት ወቅት በባዮጋዝ የተዘጋጀ ምግብ፣ ቡናውም እንዲሁ ከፊታችን በባዮጋዝ ኃይል ፈልቶ ቀረበልን፡፡ በባዮጋዝ ኃይል አማካኝነት ሙዚቃም ከፍተው ነበር፡፡ በባዮጋዝ ተጠቃሚ የሆኑት የአካባቢው ነዋሪዎች ለቤታቸው የመብራት አገልግሎት ከማግኘታቸው ባለፈ ለከብቶች መኖ የሚውለው የመቆራረጫ መሣሪያም በባዮጋዝ ኃይል ታግዞ ጥቅም እየሰጠ ነበር፡፡

በበርፌታ ቶኮፋ አካባቢ የባዮጋዝ ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል ወይዘሮ እመቤት አዱኛ አንዷ ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት በባዮጋዝ መጠቀም ከጀመሩ ሁለት ወራቸው ነው፡፡ እንደቀድሞ ማገዶ ለማዘጋጀት አይጨነቁም፡፡ ምግብ ለማዘጋጀትም በማለዳ መነሳት አይጠበቅባቸውም። ልጆቻቸውም ቁርስ በመጠበቅ ትምህርት ቤት አይረፍድባቸውም፡፡

ልጆች ሻይ የማይጠጡበት ጊዜም ነበር፡፡ ባዮጋዝ መጠቀም ከጀመሩ በኋላ ግን በፍጥነት የሚፈልጉትን ነገር ለመሥራትና ድካም በመቀነስ እፎይታ ሰጥቷቸዋል። ልጆቻቸው መብራት ባለመኖሩ ማታ ለማጥናት ትልቅ ችግር እንደነበረባቸው ያስታወሱት ወይዘሮ እመቤት፤ የሚሰጣቸውን የቤት ሥራ ለመሥራትም ሆነ ለማጥናት የነበረባቸው ችግር ተቃልሎላቸዋል፡፡ ባዮጋዝ እንደ ኤሌክትሪክ መብራት ይጠፋል፡፡ ይቆራረጣል ብለው አያስቡም፡፡ በፈለጉት ሰዓት ለኩሰው መጠቀም መቻላቸው ሌላው ትልቁ ጥቅማቸው እንደሆነም ገልጸውልናል፡፡

ወይዘሮ እመቤት ከአካባቢው የመጀመሪያዋ ተጠቃሚ እንደመሆናቸው፤ የነበረውንም ሂደት እንዲህ ነግረውናል፤ ፈቃደኝነታቸውን ሲጠየቁ የተቀበሉት በደስታ ነበር፡፡ ወቅቱ ክረምት ስለነበር ጭቃ በመሆኑ የተከላ ሥራ መሥራት ባለመቻሉ የሚሠሩት ሰዎች ትተው በመሄዳቸው ተናድደው ነበር፡፡ ዘግይቶም ቢሆን ግን ተጠቃሚ መሆን በመቻላቸው ደስታ ተሰምቷቸዋል።

ቦታ ከማዘጋጀት ውጭ ምንም አይነት ወጪም እንዳላወጡ የተናገሩት ወይዘሮ እመቤት፤ የባዮጋዝ ተጠቃሚ ለመሆን ፍቃደኝነትና ዝግጁ መሆን፤ በቅድሚያም ሥልጠና መውሰድ እንደሚጠበቅና ሥልጠናውን የወሰዱትም ባለቤታቸው እንደሆኑ ነግረውናል፡፡ እርሳቸውም በሂደት ስለአጠቃቀሙ ለማወቅ ጊዜ አልወሰደባቸውም፡፡ በበጋ ወቅት የመኖ እጥረት በመኖሩ እበት በሚፈለገው መጠን ማግኘት ግን ችግር እንደሆነ ነው ወይዘሮ እመቤት የገለጹልን፡፡

‹‹ጥቅሙን የሚያውቀው ያየ ነው፡፡›› በማለት፤ ሀሳባቸውን ያካፈሉን ሌላዋ የመንደሩ ነዋሪ ወይዘሮ የሺእመቤት ሰለሞን ናቸው፡፡ በርፌታ ቶኮፋ ተወልደው ያደጉበት፤ ተኩለው የተዳሩበትና የቤተሰብ ኃላፊ የሆኑት በእዚሁ አካባቢ ነው። እዚህ እስኪደርሱ ድረስ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂን አላዩም፡፡ ተድረው ከቤት እስኪወጡ ድረስ ቤተሰባቸውን ለማገዶ የሚሆን እበት በመጠፍጠፍ፣ ማገዶ ለቅመው በማዘጋጀት፣ በአጠቃላይ የማጀቱን ሥራ ሲያግዙ እንደነበርና ትዳር ከያዙም በኋላ በተመሳሳይ እርሳቸውም በድካም ውስጥ እንዳለፉ አጫወቱን፡፡

ከቤተሰባቸው ጀምሮ ድካሙን ስለሚያውቁት የባዮጋዝ ተጠቃሚ መሆናቸው አስደስቷቸዋል፡፡ ‹‹ድካም ቀርቶልኝ፣ ልጆቼም በሰዓቱ ምግብ አገኙ፣ ልብሴም አይቆሽሽም፣ እሳት አይለበልበኝም፤ የተጠቀምኩት እረ ብዙ ነው፡፡›› ሲሉ በደስታ ይናገራሉ፡፡ የባዮጋዝ ተጠቃሚ መሆናቸው ጊዜ እንዲያገኙ እንዳደረጋቸውና ያተረፉትንም ጊዜ ቤት በማጽዳትና የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮቻቸውን እንደሚያከናውኑበት ገልጸውልናል፡፡

ስለአጠቃቀሙም ወይዘሮ የሺእመቤት እንደነገሩን፤ አራት ጀሪካን እበት በስምንት ጀሪካን ውሃ በመበጥበጥ ለተወሰነ ደቂቃ ካስቀመጡ በኋላ የሚጣራ ቆሻሻ ካለ አጣርተው ለኃይል ማስተላለፊያ ወደ ተዘጋጀው ይገለብጣሉ። ሥራ የሚጠይቅ ቢሆንም ኩበት እንደመጠፍጠፍና ማገዶ እንደመልቀም፣ በጭስ ከመጎዳት ጋር ለንጽጽር እንደማይቀርብ ነው ያስረዱት፡፡

የማገዶ ማብሰያ ለመጠቀም እሳት ለማያያዝ በትንፋሽ መጠቀም ግድ እንደሆነና ይህም ከመተንፈሻ አካል ጋር በተያያዘ ለጤና ችግር እንደሚያጋልጥ ከተሞክሯቸው የነገሩን ወይዘሮ አስካለ ደጉ፤ እንዲህ ካለው የጤና ችግር የሚታደጋቸው የባዮጋዝ አገልግሎት ማግኘታቸው እንደሌሎች ጎረቤቶቻቸው ሁሉ እርሳቸውም ተደስተዋል። ‹‹እንግዳ ቢመጣብኝ፣ ወደ መንገድም ፈጥኜ ለመሄድ ባስብ ገና እሳት አያይዤ የሚል ጭንቀት የለም፡፡ ምድጃዬን ለኩሼ የሚያስፈልገኝን ሁሉ ተጠቅሜ ጉዳዬን መፈጸም እችላለሁ፡፡ እንግዳዬንም አስተናግዳለሁ፡፡›› ይላሉ፡፡

እንዲህ ጊዜያቸውን የሚቆጥብና ድካማቸውን የሚያቃልላቸው ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንሆናለን ብለው አስበው እንደማያውቁ የሚናገሩት ወይዘሮ አስካለ፤ ረጅሙን ጊዜ በችግር ቢያሳልፉም አሁን ማግኘታቸውም አልረፈደም ይላሉ፡፡ ሌሎች ተጠቃሚ ያልሆኑ የአካባቢያቸው ሰዎች እንደርሳቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተመኝተውላቸዋል፡፡

በባዮጋዝ እየተጠቀሙ ያሉት ወጥ ለመሥራትና ቡና ለማፍላት ብቻ እንደሆነ የገለጹልን ወይዘሮ አስካለ፤ እንጀራ መጋገር አለመቻላቸው ምክንያቱ ምን እንደሆነ እንዳላወቁት ይናገራሉ፡፡ ባዮጋዝ መጠቀም ከጀመሩ ገና አጭር ጊዜ በመሆኑ ወደፊት እንደሚጠቀሙ ተስፋ አድርገዋል፤ ‹‹አካባቢው ላይ እንግዶች በዝተው ሲያዩና የተጠቀሙ ሴቶችም ደስታቸውን ሲገልጹ በማየታቸው ደስ ብሏቸው መገኘታቸውን ይናገራሉ፡፡

‹‹ምን ተባለ? የሚለውን ከሌሎች ከምሰማ በአካል ተገኝቼ እራሴው ባረጋግጥ ይሻላል ብዬ የመጣሁት ማንም ሳይጠራኝ ነው›› በማለት በስፍራው መገኘታቸውን የነገሩን የ65 ዓመት የእድሜ ባለፀጋ ወይዘሮ ጅሩ በዳዳም የዚሁ አካባቢ ነዋሪ ናቸው። ወይዘሮ ጅሩ ስለባዮጋዝ ጥቅም ገና ማወቃቸውን ነው የነገሩን፡፡ በተለይ እንደርሳቸው አቅመ ደካማ ለሆኑ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ መገንዘባቸውንም ነው የገለጹልን። ‹‹የገጠሯን ሴት ድካምና ጫና ለመቀነስ አስበው እንዲህ ያለውን ጥሩ ሥራ የሠሩ ሰዎች ሊመሰገኑ ይገባል›› ብለዋል፡፡

ወይዘሮ ጅሩ እንዳጫወቱን፤ ባለፈው ሥርዓት የሴቶች ሊቀመንበር ሆነው ለ17 ዓመታት በሦስት ቀበሌ ውስጥ ተዘዋውረው ሲሠሩ እንዲህ ያለ ቴክኖሎጂ አላጋጠማቸውም። ያኔ ኖሮ ቢሆን ከራሳቸው አልፈው ብዙዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ ያኔ በኃላፊነታቸው ዘመን በአካባቢው ላይ የመፀዳጃ ቤት እንዲሠራ፣ የመጠጥ ውሃ እንዲገባ፣ የደን ልማት ሥራ ላይ በስፋት ይንቀሳቀሱ ነበር፡፡

እንዲህ እንደ ወይዘሮ ጅሩ ያሉ ለመጠቀም ማንንም አንጠይቅም ብለው ከመንደራቸው የመጡ ሁሉ በታደሙበት የበርፌታ ቶኮፋ መንደር ነዋሪዎች የባዮጋዝ ተጠቃሚ መሆናቸው በይፋ ተበሰረ፡፡ በአውሮፓ ኅብረት የገንዘብ ድጋፍ በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር እየሠራ የሚገኘው ኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ (SNV) የተባለ ድርጅት የበርፌታ ቶኮፋ መንደር ነዋሪዎችን የባዮጋዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስቻለ።

በኤስ ኤን ቪ ኢትዮጵያ በባዮጋዝ ፕሮግራም የፕሮዳክት ዲቨሎፕመንት ኳሊቲ ማኔጅመንት ቲም ሊደር አቶ ተስፋዬ ዓለማየሁ ስለአጠቃላይ ፕሮግራሙ እንደነገሩን፤ ባዮጋዝ ኢትዮጵያ ውስጥ የተጀመረው እ.ኤ.አ 2008 ነው፡፡ በዚህም ቴክኖሎጂውን ኢትዮጵያ ውስጥ በማምጣት ኤስ ኤን ቪ ትልቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል። ወደ ትግበራ ከመገባቱ በፊትም ፕሮግራም አተገባበር ሰነድ የተዘጋጀ ሲሆን፤ በአፍሪካ ደረጃ የአፍሪካ ባዮጋዝ ተብሎ ኢትዮጵያ፣ ኬኒያ፣ ዩጋንዳ፣ታንዛኒያና ቡርኪናፋሶ ሀገሮችን ያካተተ ፕሮግራም ነበር፡፡

እ.ኤ.አ ከ2008 እስከ 2017 ድረስ የተካሄደው ፕሮግራም በኔዘርላንድ መንግሥት እና በተለያዩ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ የታገዘ ነበር፡፡ ከ2017 ጀምሮ ደግሞ እስካሁን ድረስ ላለው ለሁለተኛው ምዕራፍ የአውሮፓ ኅብረት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር የሁለትዮሽ ፈንድ በማድረግ በጋራ ፕሮግራሙን ሲያስኬዱ ቆይተዋል፡፡

በእነዚህ ጊዜያቶች የተለያዩ የተሻሻሉ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂዎች በመተግበር አሁን ላይ ስድስተኛውን የባዮጋዝ ዲዛይን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት የተከናወነ ሲሆን፣ እስካሁንም ከ180ሺ በላይ ሰዎችን ተጠቃሚ ያደረገ ወደ 25ሺ ባዮጋዝ ተሠርቷል። የገጠሯ ሴት ለማብሰያ በምትጠቀመው ማገዶ ለሳንባ በሽታ፣ ለዓይን ትራኮማና ለተለያየ የጤና ችግር ተጋላጭ የምትሆንበትን ሁኔታ በማስቀረት፣ የአካባቢ ብክለትንም በመቀነስ፣ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለመጨመርም ባዮጋዝ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አቶ ተስፋዬ ያስረዳሉ፡፡

ባዮጋዝ ለመብራት አገልግሎት ከመዋሉ በተጨማሪ ተረፈ ምርቱ ለተለያየ የሰብል ልማት በማዋል አርሶአደሩ ለማዳበሪያ ግዥ የሚያወጣውን ወጪ ለመቀነስ እንደሚያግዘውም አስረድተዋል፡፡ ይህ የሁለተኛው ምዕራፍ እ.ኤ.አ 2024 ላይ እንደሚያበቃ የጠቆሙት አቶ ተስፋዬ፤ ፕሮግራሙ ለገጠሩ ማኅበረሰብ ጠቃሚ በመሆኑ ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ብለዋል፡፡ እስካሁን በተሠሩት ሥራዎች በሀገር ውስጥ ሙያተኞችን ማፍራት በመቻሉ መንግሥት ሥራውን በማስቀጠል እንደሚያጠናክር ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡ ቴክኖሎጂ ነፃ እንዳልሆነና የማኅበረሰብ ተሳትፎም እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል። እስካሁንም የተሠሩት ሥራዎች በለጋሾች፣ በመንግሥትና በማኅበረሰብ ተሳትፎ የተሳኩ መሆናቸውንና ይኸው ሊጠናከር እንደሚገባ ገልጸዋል።

የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ አካባቢው ላይ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና ማኅበረሰቡ በአግባቡ እንዲጠቀምበት እየተሠራ ስላለው ሥራም በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሸዋ ዞን የውሃና ኢነርጂ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ገዛኸኝ ታፈሰ ገልፀውልናል፡፡ በምዕራብ ሸዋ ዞን ወልመራ ወረዳ ባዮጋዝ በመጠቀም ሞዴል ወረዳ መሆኑንም አመላክተዋል፡፡

ከወረዳው አንዱ የሆነው በርፌታ ቶኮፋ ቀበሌ በሞዴልነት የተመረጠው ሌሎች ቀበሌዎችም ተጠቃሚ ከመሆናቸው በፊት ተጠቃሚ በመሆኑ ነው ብለዋል። ቀበሌው ሞዴል የሆነው ፕሪፋብሪኬትድ የሚባለው አዲስ የባዮጋዝ ቴክኖሎጂ መግባቱንም ጨምር መሆኑን አስታውሰው፤ ቀደም ሲል በሲሚንቶ፣ አሸዋ ግብዓቶች ይሠራ የነበረው ቴክኖሎጂ በፕላስቲክ መተካቱ ቴክኖሎጂውን ለየት ያደርገዋል ብለዋል።

ግብረሠናይ ድርጅቶች ከሚያደርጉት ድጋፍ በተጨማሪ በምዕራብ ሸዋ ዞን በሚገኙ 23 ወረዳዎች ቴክኖሎጂውን ተደራሽ ለማድረግ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የጠቆሙት አቶ ገዛኸኝ፤ ከዚህ ቀደም በመንግሥት በጀት የማይያዝለት እንደነበርና በ2016ዓ.ም ግን ትኩረት ተሰጥቶ በዞኑ ለባዮጋዝ ግንባታ የሚውል ከ16ሚሊዮን ብር በላይ በጀት መመደቡን ገልጸዋል፡፡

በተለይም የኤሌክትሪክ መብራት አገልግሎት ተደራሽ ባልሆነባቸው የዞኑ አካባቢዎች የባዮጋዝ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቅድሚያ በመስጠት እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡ በዞኑ ወደ 160 ባዮጋዝ እንዲሠራ በእቅድ ቢያዝም ከእቅድ በላይ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ መሆኑንና እስካሁን ከእቅድ በላይ መሥራት የሚያስችል ሥራ መከናወኑን አመልክተዋል።

የሥራ ተነሳሽነቱ ቢኖርም ለባዮጋዙ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ገበያ ላይ ማግኘት ተግዳሮት መኖሩን አቶ ገዛኸኝ አንስተዋል፡፡ የባዮጋዝ ግንባታው የትምህርት ቤቶችንና ሌሎችም ተቋማት ተጠቃሚ እንዲያደርግ የሚሠራ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

እንዲህ ያሉ ቴክኖሎጂዎች ሥራ ላይ ሲውሉ ለመቀበል ፍቃደኛ አለመሆን፣ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ደግሞ በአግባቡ ያለመጠቀም ሁኔታ መኖሩን ያነሳንላቸው አቶ ገዛኸኝ፤ ያለመቀበሉ ሁኔታ ቀደም ሲል የነበረ ቢሆንም አሁን መቀረፉን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ባለቤቶቻቸው ፍቃደኛ ባይሆኑ እንኳን ሴቶች በራሳቸው ተነሳሽነት ተጠቃሚ በመሆን ሞዴሎችን ማፍራት መቻሉንም አመልክተዋል፡፡ አዳዲስ የቴክሎጂ ሽግግር ሲደረግ ባለሙያዎችም አብረው እንዲሠለጥኑ ባለመደረጉ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ለሚያጋጥም ችግር መፍትሔ ለመስጠት ተግዳሮት መኖሩን አቶ ገዛኸኝ አልሸሸጉም፡፡ በተቻለ መጠን ግን በክትትል ለችግሮች መፍትሔ ለመስጠት ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

ተረፈ ምርቱ ለግብርና ግብዓት መዋሉ፤ የኬሚካል ማዳበሪያን የዋጋ ውድነት ከመቀነሱ በተጨማሪ በተፈጥሮ ማዳበሪያ መጠቀም ለጤና ተስማሚ የሆነ ምርት ማግኘት ማስቻሉን ጠቅሰው፤ በዚህ መልኩ ከቀጠለ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የአፈር ለምነትን መመለስ እንደሚቻል አስረድተዋል። አርሶአደሩም ግብዓቱን ገበያ ላይ በማዋል የኢኮኖሚ ተጠቃሚ መሆን እንደቻለም አቶ ገዛኸኝ ነግረውናል፡፡

ከኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት ርቆ የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል በገጠር ኢነርጂ አማራጭ ተደራሽ ለማድረግ መንግሥት ፖሊሲና አቅጣጫ ቀርጾ እየሠራ መሆኑንም በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የገጠር ኢነርጂ ቴክኖሎጂ ልማትና ሽግግር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብርሃኑ ወልዱ ነግረውናል። ላለፉት አስር ዓመታት ከ48ሺ በላይ የባዮጋዝ ማመንጫዎች ተገንብተው ጥቅም ላይ መዋላቸውንም ገልጸውልናል፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

የትናንቱን አዲስ ዘመን አስገራሚና ታሪካዊ ዘገባዎች በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ መለስ ብለን እንመለከተዋለን። አንድ የቆየ የጋዜጣው ዘገባ ሌባይቱን ሌባ ሰረቃት ይለናል፤ የሀገር ባህል አልባሳት እያሉ አጭር ቀሚስ ለምኔ ሲል የሐረር ከተማ ፖሊስ አጫጭር ቀሚስ የሚለብሱትን ወይዛዝርት ከጣቢያው ያቀረበበትን አጋጣሚም የሚያስታውሰን ዘገባ ይዘናል፡፡ በተጨማሪም ዘመዶቼን አላስጠቀምክም በሚል ሰበብ በክራንች አራት ጥርስ ያረገፈው ጥጋበኛ ግለሰብ ለአንድ ጥርስ 2 ዓመት ተሰልቶ በስምንት ዓመት እንዲቀጣ ተበይኖበታል። የመንገደኛውን የትዝብት ደብዳቤንም በማከል ለዛሬው ቀንጭበን እናስታውስ፡፡

### ሌባይቱን ሌባ ሰረቃት

(ኢ.ዜ.አ.)፡- በግርድና ተቀጥራ ከምትሠራበት ቤት ፪ ሺህ ብር ሰርቃ ስትኮበልል፤ የሰረቀችውን ገንዘብ በሌላ ሌባ የተሰረቀችው ዘውዲቱ ሞላ ፤ በ፮ ወር እስራት እንድትቀጣ አሰላ ከተማ ያስቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት ፈረደ፡፡

ተከሳሽ ለእስራት ያበቃት ይህንኑ ገንዘብ የተሰረቀችው በአሰላ ከተማ በግርድና ተቀጥራ ትሠራበት ከነበረው አቶ ግርማ ድፋባቸው ቤት ፤ ባለፈው መጋቢት 5 ቀን 66 ዓ/ም / ሲሆን ፤ እሷ ገንዘቡን ይዛ ወደ ተጉለትና ቡልጋ አውራጃ ግዛት ከኮበለለች በኋላ ፤ ደብረ ብርሃን ከተማ ውስጥ ስትዘዋወር በጋሻው አጥላው በተባለው ልማደኛ ሌባ መሰረቋ ታውቋል፡፡

ከዚያም ዘውዲቱ ሞላ ሀብቷ በልማደኛ ሌባ መሰረቁን ለክፍሉ ፖሊስ አመልክታ፤ በተደረገው መከታተል በጋሻው አጥላው ተይዞ ምርመራው ከተጣራ በኋላ፤ ደብረ ብርሃን አስቻለው የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመቅረብ ጥፋቱ በማስረጃና በሕግ ምስክሮች በመረጋገጡ፤ አንድ ዓመት እስራት እንዲቀጣ ሲፈረድበት፤ የተሰረቀውም ገንዘብ ለባለቤቷ እንዲመለስ ታዘዘ። በዚህም መሠረት ዘውዲቱ ሞላ በፍርዱ መሠረት ገንዘቡን ለመረከብ ስትሰናዳ ዋናው ባለ ገንዘብ አቶ ግርማ ድፋባቸው በክትትል ደርሰውባት ኖሮ ፤ አስቀድሞ ገንዘብ ከሳቸው የተሰረቀ መሆኑን ማስረጃ አቅርበው ዘውዲቱ ከነገንዘቡ እጅ ከፍንጅ ተያዘች፡፡

ከዚያም ተከሳሿ ወደ አሰላ ከተማ ተልካ ወንጀሉን በፈጸመችበት ክፍል ክስ እንዲቀርብባት ተደርጎ፤ አድራጎቷ በማስረጃና በሕግ ምስክሮች በመረጋገጡ በ፮ ወር እስራት እንድትቀጣ የተፈረደባት መሆኑን አንድ የፍርድ ቤቱ ቃል አቀባይ አስታውቋል፡፡ በሁለቱ ሌቦች መቀባበል ከተሰረቀው ከዚሁም 2 ሺህ ብር ውስጥ 725 ብር ከ25 ሳንቲም ሲባክን በመጨረሻ የተገኘው ተራፊ ገንዘብ 1 ሺህ 338 ብር ከ75 ሳንቲምና በተሰረቀው ገንዘብ ተገዝተው በኤግዚቢትነት የቀረቡት ልብሶችና ዕቃዎች ለባለገንዘቡ ለአቶ ግርማ ድፋባቸው እንዲሰጡ ፍርድ ቤቱ በዚሁ ጊዜ አብሮ ማዘዙን ቃል አቀባዩ ጨምሮ ገልጧል፡፡

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 27 ቀን 1966 ዓ.ም )**

### የአጭር ቀሚስ ቁጥጥር በሐረር

ሐረር፤(ኢ-ዜ-አ-) በሐረር ከተማ ውስጥ አጫጭር ቀሚስ እየለበሱ በሚዘዋወሩት ሴቶች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር እየተደረገ መሆኑን የሐረር አውራጃ ፖሊስ አዛዥ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ ገለጡ፡፡

በተደረገው ቁጥጥር መሠረት በሐረር ከተማ ውስጥ የሀገርን ባህል የሚያጎድፍ ልብስ ለብሰው የተገኙት 67 ልጃገረዶችና ሴቶች 2ኛ ፖሊስ ጣቢያ እየቀረቡ ዳግመኛ ላለመልበስ መፈረማቸውን ሌተናል ኮሎኔል ኃይለ ሚካኤል አስረድተዋል፡፡ ይኸው አፈጻጸም ለወደፊቱ በየጣቢያው ተላልፎ በሚገባ በሥራ ላይ እንደሚውል ታውቋል፡፡

በዚሁ ይዞታ በከተማው ውስጥ ይታይ ነበረው የአጭር ቀሚስ ለባሾች ቁጥር መቀነሱንና ለወደፊት ጨርሶ እንደሚጠፋ ሌተናል ኮሎኔል ኃይለሚካኤል ገብሬ እምነታቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 2 ቀን 1962ዓ.ም)**

### ጥርስ ያወለቀ ተከሳሽ ስምንት ዓመት ጽኑ እስራት ተፈረደበት

በሰሜን ጎንደር በበየዳ ወረዳ በርዳታ እህል ክፍፍል በተነሳ ችግር ክስ የተመሰረተበት ግለሰብ የከሳሹን ጥርስ በማውለቁ በስምንት ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ የተወሰነበት መሆኑን የወረዳው ማስታወቂያ ጽ/ቤት ገለጸ፡፡

......

ፍርድ ቤቱ በሬ ፈረደ በተባለው ላይ ቅጣቱን የወሰነው ዘመዶቼን ለምን ለርዳታ አልመዘገብክልኝም ብሎ ጥያቄ ያቀረበለትን ጥፍጡ መንግሥቱ የተባለውን ግለሰብ በሚጠቀምበት የእግር ክራንች በመምታት አራት የፊት ጥርሱን በማውለቁ ነው፡፡

**(አዲስ ዘመን ታኅሳሳ 14 ቀን 1978ዓ.ም)**

### በሕጉ ነው ወይንስ በራሱ ፍላጎት?

ነሐሴ 28 ቀን 1979ዓ.ም ከሻሸመኔ ወደ ድሬዳዋ ለሚጓዘው የጎን ቁጥር 215 የሆነ የአውቶብስ ቲኪት ቆራጭ የነበሩትን ደመቁ የተባሉት ግለሰብ፤ ለ12 ዓመት ልጅ ቲኬት ለመቁረጥ በሕጉ መሠረት ሰልፍ ይዤ ተራዬ ሲደርስ ግማሽ ዋጋ ይቁረጡልኝ አልኳቸው። እሳቸውም አይቻልም ግማሽ ዋጋ የለም ይሉኛል፡፡ እሺ ይሁን በሙሉ ዋጋ ስጡኝ እላቸዋለሁ መልሰው የለም ውጣ ብለው ያፈጡብኛል፡፡ እኔም ሁኔታው ስላስፈራኝ ወደሚከተለው ክፍል በመሔድ በዝርዝር አስረዳሁ፡፡ የኔን አቤቱታ የተመለከቱትም ወደ ቦታው በመሔድ ለምን እንዲህ ሠራህ ብለው ከጠየቁ በኋላ ቲኬቱ ይቆረጥላቸው ብለው አዘዙ፡፡ ግለሰቡም መልሰው አይቻልም እስቲ የሚመጣውን አያለሁ፤ ቲኬቱም አልቋል ይሏቸዋል፡፡ አቤቱታ ሰሚውም ጥለውኝ ወደ ቢሯቸው ይመለሳሉ። ተስፋ ሳልቆርጥ አሁንም ወደዚያው ድረስ በመሔድ ሰውየው የሚሠሩት በፍላጎታቸው ወይስ በሕግ ነው ብዬ ከጠየቅሁ በኋላ ቲኬቱን ሽጬ ጨርሻለሁ ማለቱስ ተገቢ ነው? ግማሽ ዋጋስ እስከስንት ዓመት ልጅ ነው የሚቆረጠው ብዬ ጥያቄዬን አቀረብኩ። በዚህን ጊዜ ወደ ቦታው በመሔድ በሕግ ሳይሆን በልመና በሙሉ ሂሳብ ቲኬት እንዲቆርጥልኝ አድርገው ሐጻኑን ልልከው ችያለሁ። ሥነ ሥርዓት የጎደላቸውና በሕዝብ የሚያሾፉ እነዚህን መሰል ሠራተኞች ሊታረሙ ይገባል፡፡ የሕዝብ ማመላለሻ ኮርፖሬሽንስ ለምንድነው ጅራታቸውን እየያዘ ልክ የማያስገባልን?

**(አዲስ ዘመን ጳጉሜ 4 ቀን 1979ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## በ2024 የዓለምን ፖለቲካ የሚወስኑ ከ40 በላይ ምርጫዎች ይካሄዳሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ከቀናት በኋላ በሚገባው የጎርጎሪሳውያኑ 2024 አዲስ ዓመት የዓለምን ፖለቲካ የሚወስኑ ከ40 በላይ ምርጫዎች ይካሄዳሉ፡፡ አሜሪካ፣ ሩሲያ፣ ዩክሬን፣ እስራኤል፣ ታይዋን እና ሕንድ ምርጫ ከሚያካሂዱ ሀገራት መካከል ዋነኞቹ ናቸው

የዛሬ ሳምንት ሰኞ እለት በሚገባው የ2024 አዲስ ዓመት 40 በመቶ የዓለማችን ሕዝቦች የሚያስተዳድራቸውን መንግሥት ለመወሰን ድምፅ ይሰጣሉ የተባለ ሲሆን አሜሪካ፣ ሩሲያ፣ ኢራን፣ እስራኤል፣ ታይዋን፣ ሕንድ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ሌሎችም ሀገራት ምርጫ ከሚደረግባቸው ሀገራት መካከል ዋነኞቹ ናቸው፡፡

በጦርነት፣ በረሀብ እና በድህነት ስሟ ተደጋግሞ የሚነሳው አፍሪቃ በመገባደድ ላይ ባለው እ.አ.አ. 2023 በርካታ ክስተቶችን አስተናግዳለች። በመጭው 2024 ከሚጠበቁ ክስተቶች አንዱ ምርጫ ነው። ደቡብ አፍሪካን ጨምሮ በአፍሪካ በመጭው ዓመት ብዙ ምርጫዎች ይደረጋሉ።

በጎርጎሪያኑ በየካቲት 2024 ከሚካሄደው ምርጫ በፊት በሴኔጋል ሕዝባዊ ተቃውሞዎች ከወዲሁ ተቀስቅሰዋል። ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል ግፊቱን ለማርገብ ለሦስተኛ ጊዜ ከእጩ ከመሆን ተቆጥበው ጠቅላይ ሚኒስትር አማዱ ባን ወደ ውድድር ልከዋል።

የምርጫዎቹ ውጤት የዓለምን የፖለቲካ እና ዲፕሎማሲ አሰላለፍ ሊቀይሩ ይችላሉ የተባለ ሲሆን የምርጫዎቹ ውጤቶች እና ወደ ሥልጣን የሚመጡት ተመራጮች አዳዲስ ውሳኔዎችን ሊወስኑ እንደሚችል አል አይን ዘግቧል።

ለታይዋን ሙሉ ነፃነት ለማረጋገጥ የሚሠራው ፓርቲ በምርጫው አብላጫ ድምፅ ካገኘ ቻይና ጣልቃ ለመግባት ስትሞክር ከአሜሪካ ጋር ወደ ጦርነት ልትገባ እንደምትችል ተሰግቷል፡፡

ሌላኛው ምርጫ የሚካሄድበት ሀገር እስራኤል ትሆናለች የተባለ ሲሆን በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ አመራር ደስተኛ ያልሆኑ ዜጎች መበራከትን ተከትሎ አዲስ መሪ ሊመጣ ይችላል ተብሏል፡፡

ሌላኛዋ ምርጫ የሚደረግባት ሀገር ሩሲያ ስትሆን ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ለአምስተኛ ጊዜ ተወዳድረው ምርጫውን እንደሚያሸንፉ ይጠበቃል።

በጦርነት ውስጥ ያለችው ዩክሬን የፊታችን መጋቢት ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ለማካሄድ ፕሮግራም የያዘች ሲሆን አዲስ ፕሬዚዳንት ሊመጣ ይችላል ተብሏል፡፡

አፍሪካዊቷ ደቡብ አፍሪካ የፊታችን ሚያዝያ ወር ላይ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ የምታካሂድ ሲሆን ላለፉት 30 ዓመታት ሥልጣን በአብላጫ ይዞ የቆየው ኤኤንሲ ፓርቲ ሊሸነፍ እንደሚችል ተሰግቷል፡፡

ግንቦት ላይ ደግሞ የዓለማችን ቁጥር አንድ ባለ ሕዝብ ብዛት ባለቤት የሆነችው ሕንድ በታሪክ ግዙፉን ምርጫ እንደምታካሂድ ሲገለጽ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ የ28 ፓርቲዎች ጥምረት በሆነው የሕንድ ብሔራዊ ጥምረት ለልማት ፓርቲ የመሸነፍ እድላቸው ሰፊ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

በሕንድ አዲስ መሪ ወደ ሥልጣን የሚመጣ ከሆነ አሜሪካ ቻይናን በእስያ ለመገዳደር በያዘችው እቅድ ላይ እንቅፋት አልያም ምቹ ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ተብሏል፡፡

ሌላኛዋ ምርጫ የምታካሂደው ሀገር ብሪታንያ ስትሆን ያለባትን የጠቅላይ ሚኒስትሮች አለመረጋጋት ምላሽ እንደምትሰጥ ተጠብቋል፡፡




ከዚህ በተጨማሪም በኦስትሪያ፣ ቤልጂየም፣ ክሮሺያ እና ፊንላንድ ምርጫ ያካሂዳሉ የተባለ ሲሆን የአውሮፓ ፓርላማ አባላት ምርጫም ይካሄዳል፡፡

በአውሮፓ የሚደረጉ ምርጫዎች በቀኝ ዘመም ወይም ስደተኞችን የሚጠሉ ፓርቲዎች ሥልጣን እየተቆጣጠሩ በመምጣት ላይ ናቸው፡፡

አስቀድማ በሴት ፕሬዚዳንት እንደምትመራ ያረጋገጠችው ሜክሲኮ ሐምሌ ላይ በሚካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ላይ ሁለት ሴት እጩ ፕሬዚዳንቶች ይወዳደራሉ ተብሏል፡፡

የዓመቱ የመጨረሻ ምርጫ የሚካሄደው በአሜሪካ ሲሆን ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን እና ዶናልድ ትራምፕ የመጨረሻ እጩ ሆነው እንደሚቀርቡበት ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል በሥልጣን ላይ ባሉት መንግሥታት አለመርካትም በአንዳንድ የአፍሪካ ሃገራት ሥልጣን ወደ ተቃዋሚዎች እንዲሸጋገር ሊያደርግ ይችላል የሚል ግምት ተሰጥቶታል።

የሩስያ እና የቻይና ሁኔታ የአፍሪካ ሀገራትን በማጠናከር ሥራ በዴሞክራሲ ላይም ተፅዕኖ እንዳለው የዘርፉ የባለሙያዎች ይጠቅሳሉ። ከዚህም ባሻገር የምዕራቡን ዓለም የበላይነት ለመግታት እና በአህጉሪቱ ላይ ኃያላኑ የበለጠ ተፅዕኖ ለመፍጠር እየተፎካከሩ ይገኛል።

አሜሪካና የአውሮፓውያን በበኩላቸው ባላቸው ተፅዕኖ የተነሳ በአፍሪካና በእስያ ሀገራት በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ የእራሳቸው ጫና እንደሚኖራቸው ይገመታል ሲሉ የፖለቲካ ተንታኞች ሃሳባቸውን አስቀምጠዋል።

# ስፖርት



# የኢትዮጵያ ዋንጫ የሩብ ፍፃሜ ተፋላሚዎች ተለይተዋል

ዓለማየሁ ግዛው

አንጋፋው የኢትዮጵያ ዋንጫ ለረጅም ዓመታት ተቋርጦ ዘንድሮ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ውድድሩ ባለፉት ሳምንታት በተለያዩ ዙሮች ሲካሄድ መቆየቱ የሚታወቅ ሲሆን የ3ኛ ዙር ጨዋታዎችን አስተናግዶም ሩብ ፍጻሜ የተቀላቀሉ ክለቦችን በመለየት ወደ ወሳኝ ምዕራፍ ተሸጋግሯል፡፡ የሩብ ፍጻሜ ጨዋታዎችም የካቲት ወር ላይ የሚካሄዱ ይሆናል፡፡

የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግና የታችኛውን የሊግ እርከን ክለቦችን አካቶ እየተከናወነ የሚገኘው የዘንድሮ የኢትዮጵያ ዋንጫ ውድድር ባለፉት ሦስት ዙሮች ያልተጠበቁ ውጤቶችን አስተናግዷል፡፡ የውድድሩ ሦስተኛ ዙር ጨዋታዎች ከኅዳር 11 ጀምሮ በአዲስ አበባ፣ አዳማና ሃዋሳ ከተሞች ተካሂደው በጠንካራ ፉክክሮች ታጅበው ነው የተጠናቀቁት፡፡

ለአራት ተከታታይ ቀናት ሁለት ሁለት ጨዋታዎችን በቀን እያስተናገደ ከትላንት በስቲያ በተጠናቀቀው የ3ኛው ዙር ውድድር የተለያዩ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በአብዛኛው ጠንካራ የሚባሉ የፕሪሚየር ሊጉ ክለቦችም ተጋጣሚዎቻቸውን በመርታት ወደ ወሳኙ ምዕራፍ ማለፍ ችለዋል፡፡

በመጀመሪያው ቀን ጨዋታ ነገሌ አርሲ ከሊጉ ጠንካራ ተፎካካሪ ክለብ ኢትዮጵያ መድን ተጫውቶ ኢትዮጵያ መድን 2 ለ 1 አሸናፊ ሆናል፡፡ ለኢትዮጵያ መድን ግቦቹን በርናንድ ኦቼንግና ቻክዋሜ ጎድሰን ሲያስቆጥሩ የነገሌ አርሲን ብቸኛ ግብ ታምራት ኢያሱ ማስቆጠር ችሏል፡፡ ሌላኛው ደብረብርሃን ከተማን ከፋሲል ከነማ ያገናኘው ጨዋታ በፋሲል ከነማ 1ለ 0 አሸናፊነት ሲጠናቀቅ ብቸኛዋን የማሸነፊያ ግብ ፍቃዱ ዓለሙ በፍጹም ቅጣት አስቆጥሯል፡፡ ይሄንን ውጤት ተከትሎ ፋሲል ከነማና ኢትዮጵያ መድን የሩብ ፍጻሜውን ተቀላቅለዋል፡፡

በሁለተኛው ቀን የመጀመሪያ መርሐግብር ባሕርዳር ከተማ ከአርባምንጭ ከተማ ተገናኝተው አዞዎቹ 1 ለ 0 በሆነ ጠባብ ውጤት አሸንፈው ሩብ ፍጻሜ መግባት ችለዋል፡፡ ብቸኛዋን ግብ አሕመድ ሁሴን ከመረብ አሳርፏል፡፡ ቢሾፍቱ ከተማ ከአዳማ ከተማ ያደረጉት ጨዋታ በአዳማ ከተማ 3 ለ 1 አሸናፊነት ሲጠናቀቅ ቦና አሊ ሁለት ግቦችን ሲያስቆጥር አሸናፊ ኤልያስ ቀሪዋን ግብ አስቆጥሯል። ቢሾፍቱን ከመሸነፍ ያልታደገችውን ብቸኛ ግብ ሲሳይ አማረ ከመረብ አሳርፏል፡፡ በዚህም መሠረት አዳማ ከተማና አርባምንጭ ከተማ ሩብ ፍጻሜውን የተቀላቀሉ ክለቦች መሆን ችለዋል፡፡

ቅዳሜ እለት የተካሄዱ ሁለት ጨዋታዎች በግቦች የተንበሸበሹ ውጤቶች ተመዝግበውባቸዋል። በነዚህ ጨዋታዎች 14 ግቦች ከመረብ አርፈዋል። የሊጉን ሁለት ክለቦች ያፋለመው የሀድያ ሆሳዕና እና ወላይታ ድቻ ጨዋታ በወላይታ ድቻ 5 ለ 2 አሸናፊነት ተጠናቋል፡፡ ቢንያም ፍቅሬ 2 ሁለት ጎሎችን ሲያስቆጥር፣ አብነት ደምሴ፣ ዮናታን ኤልያስ እና ዘላለም አባተ ቀሪዎቹን ጎሎች ለወላይታ ድቻ አስቆጥረዋል፡፡ ሀድያን ከሽንፈት ያልታደጉትን ሁለት ግቦችን መለስ ሚሻሞ አስቆጥሯል፡፡

በጎል የተንበሸበሸው ሌላው ጨዋታ ፈረሰኞቹን ከ አዲስ የሊጉ አዳጊ ክለብ ሻሸመኔ ከተማ ያገናኘ ሲሆን ቅዱስ ጊዮርጊስ 5 ለ 2 በሆነ ውጤት አሸንፏል፡፡ ለቅዱስ ጊዮርጊስ አቤል ያለው 2 ጎሎችን ሲያስቆጥር፤ ቢንያም በላይ፣ ሄኖክ አዱኛና አማኑኤል ኤርቦ ቀሪዎቹን ጎሎች ማስቆጠር ችሏል፡፡ ይሄን ውጤት ተከትሎ ወላይታ ድቻና ቅዱስ ጊዮርጊስ ቀጣዩን ዙር ተቀላቅለዋል፡፡







**የፕሪሚየርሊጉ ታላላቅ ክለቦች የኢትዮጵያ ዋንጫ ሩብ ፍፃሜን ተቀላቅለዋል፣**

በሦስተኛ ዙር ማጠናቀቂያ ቀን በተካሄዱ ጨዋታዎችም ሁለት ሩብ ፍጻሜውን የተቀላቀሉ ክለቦች ተለይተዋል፡፡ ሀዋሳ ከተማ ከመቻል ያካሄዱት ጨዋታ በመቻል 3 ለ 0 አሸናፊነት ተጠናቋል፡፡ ዓሊ ሱለይማን ሦስቱንም ግቦች በማስቆጠር ሃትሪክ መሥራት ችሏል፡፡ ውጤቱን ተከትሎ ሀዋሳ ከተማ ወደ ቀጣይ ዙር ማለፍ ችሏል፡፡ ኮልፌ ቀራኒዮ ክፍለ ከተማ ከ ኢትዮጵያ ቡና ያካሄዱት ጨዋታ በቡናማዎቹ 2 ለ 0 አሸናፊነት ሲጠናቀቅ፤ ጎሎቹን ማሐመድ ኑር ማስቆጠር ችሏል፡፡ ኢትዮጵያ ቡና ቀጣዩን ዙር የተቀላቀለ የመጨረሻው ክለብም ሆኗል።

እነዚህን ውጤቶች ተከትሎ የሩብ ፍጻሜ ጨዋታዎች ድልድል ይፋ የተደረገ ሲሆን በየካቲት ወር ወደፊት በሚገለጽ ቀንና ቦታ ጨዋታዎቹ እንደሚካሄዱ ተገልጿል፡፡ በዚህም መሠረት ተጋጣሚዎቻቸውን በከፍተኛ ብልጫ በማሸነፍ ሩብ ፍጻሜውን የተቀላቀሉት ቅዱስ ጊዮርጊስና ወላይታ ድቻ እርስ በርስ የሚገናኙ ሲሆን የሚያደርጉት ፉክክር በጉጉት ይጠበቃል፡፡ አዳማ ከተማ ከኢትዮጵያ መድን የሚያካሄዱት ጨዋታ ሌላኛው ጠንካራና የብዙዎችን ትኩረት የሚስብ ይሆናል፡፡ አርባምንጭ ከተማን ከሀዋሳ ከተማ ያገናኘው ድልድልም ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ፋሲል ከነማን ከኢትዮጵያ ቡና የሚያገናኘው ጨዋታም ሁለት ጠንካራና ባለብዙ ደጋፊ ክለቦችን ያፋጠጠ ሆኗል፡፡


## የስብሰባ ጥሪ

ጭድ ተራ አጠቃላይ ንግድ አክስዮን ማህበር ቅዳሜ ጥር 4 2016 ዓ.ም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በድል በትግል አዳራሽ ከጠዋቱ 2:30 ጀምሮ የ2016 ዓ.ም የመጀመሪያውን አስቸኳይ እና መደበኛ ጉባኤ ስብሰባ ስለሚያደርግ ማናቸውም የአክስዮን ማህበሩ አባላት በዕለቱ ተገኝታችሁ የስብሰባው ተካፋይ እንድትሆኑ በጥብቅ ያሳስባል፡፡ በተጨማሪም በስብሰባው የሚወሰነው ውሳኔዎች በሙሉ በመተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 24 (ሃያ አራት ) መሠረት በስብሰባው ባልተሳተፉትም የአክስዮን አባል ላይ ጭምር ተግባራዊ እንደሚሆን ከወዲሁ ማስገንዘብ እንወዳለን፡፡

### የመደበኛ ስብሰባ አጀንዳዎች

* የስብሰባ አጀንዳዎችን ማጽደቅ
* በተጓደሉ የቦርድ አባላት ምትክ ቦርዱ በእጩነት ያቀረባቸውን ማጽደቅ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው ምርጫ ማካሄድ
*የተመረጡትን ማሟያ የቦርድ አባላት ምርጫ ማፅደቅ
* የሥራ አመራ ቦርድ ሪፖርት ማፅደቅ

### የአስቸኳይ ስብሰባ አጀንዳዎች

* አክስዮን ማህበሩ የሚቀበላቸው የአዲስ አባላት የአክስዮን 18,900,000.00 (አስራ ስምንት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሺ ብር) ማመንጨት
*አክስዮን ማህበሩ ያመነጫቸውን አክስዮኖች ለአዲስ አባላት በሽያጭ ማስተላለፍ
* የስብሰባ ቃለ ጉባኤ ውሳኔዎችን ማፅደቅ

**ማሳሰቢያ፡-**

በስብሰባው ላይ መገኘት የሚችል የአክስዮን ማህበሩ አባል ብቻ ሲሆን ሕጋዊ ውክልና አለን የምትሉ የአክስዮን ማህበሩ አባል ወኪሎች የውክልና ማረጋገጫችሁን ይዛችሁ መገኘት እንዳለባችሁ በቅድሚያ እናሳውቃለን፡፡

**የጭ/ተ/አ/ን/አ/ማህበር ቦርድ**

## የኦዲት ሥራ ጨረታ ማስታወቂያ

በሕዝብ ተሳትፎ የተቀነባበረ ዘላቂ የልማት ድርጅት(ሲቢሲዶ) ከኢፌዴሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን በምዝገባ ፍቃድ ቁጥር 1393 የኢትዮጵያ ነዋሪዎች የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በመሆን ተመዝግቦና ህጋዊ ፍቃድ አግኝቶ የሚንቀሳቀስ የዕርዳታ ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ የ2023 በጀት ዓመት ሒሳብ በኦዲት ሥራ ህጋዊ ፍቃድ ያላቸውን ድርጅቶች አወዳድሮ ማሠራት ይፈልጋል፡

**ስለሆነም፡-**

1. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ኦዲት በማድረግ ልምድ ያለው
2. የ2016 የታደሰ ፍቃድ ያለው
3. የሚሠራበትን ዋጋና የሚያስረክብበትን ጊዜ በመጥቀስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በድርጅቱ መሥሪያቤት በአል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ስምንት የሥራ ቀናት ድረስ በመላክ መወዳደር ይችላሉ፡፡

**አድራሻ፡-** ልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 ከበርበሬ በረንዳ ዋልያ ስቲል ሕንፃ ከፍ ብሎ ባለው መንገድ በግምት 200 ሜትር ገባ ብሎ ይገኛል፡፡

**ለበለጠ መረጃ፡ስልክ ቁጥር 0989-505050 ወይም 0917902341**

**በሕዝብ ተሳትፎ የተቀነባበረ ዘላቂ የልማት ድርጅት(ሲቢሲዶ)**

## ደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 03 የቤት ቁጥር 2397 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0043000167 ዳንኤል ተስፋማሪያም በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የተርን አቨር ታክስ / ቲኦቲ/ እጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ቁጥር 001 የተሰራበት እና ከቁጥር 002 እስከ 00100 ያልተሰራበት ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀስው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ቦሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ዳንኤል ተስፋማሪያም**